በገዳም የሚኖሩ ሰዎች በመንፈስ እድገታቸው በግብራቸው፥ ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው የመንፈስ ፍሬዎች የተባሉትን ለማፍራት እንደለሰለሰችው መልካም መሬት መሆናቸውን እነ ፓስተር ዳዊት ሊረዱ ይገባቸዋል:: ይህ ጾጋ የተመላው ገዳማዊ ቅጠላ-ቅጠል ምግብ፥ ለሰው ልጅ ሁሉ የታዘዘ እንደሆነ ሳይረዳ፥ ያገኘውን ሁሉ ለመብላት በመሻማት ያለው ፓስተር ዳዊት እራሱን አጽድቆ፥ ተኮነኑ እያለ በገዳማውያን አባቶች ላይ የሚያውጀው ጂሀድ የሰማ ሁሉ ሊገስጸውና ሊአሳፍረው የክርስትናና የሞራል ግዴታ አለበት:: መጻሕፍት እያስተማሩ ያሳደጉን ሊቃውንት አበው፥ ለተለያዩ አገልግሎቶች በቤተ መቅደስና በአውደ ምሕረት ላይ በሕዝብ ፊት የምንቆም ሁሉ፥ ሕዝቡ ከስቶ ተጎሳቁሎ ጠቁሮ ሳለ፥ ቀልተን ወፍረንና ደንደሳችን አብጦ እንዳንታይ ነበር:: ይህ ደግሞ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ባሕልና መመሪያ ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስ ከነብያትና ከሐዋርያት የመጣ ስለሆነ ከተቻለ የሁሉም ቢሆን ምሳሌነቱ ጠቃሚ ነው::

ፓስተር ዳዊትም እመቤታችን ስሙት ብላ ያዘዘችውንም ባለመረዳቱ "ሥጋየን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" የሚለውን የክርስቶስን አዋጅ መስማት አልቻለምና፥ "የጤፍ እንጀራ ባለመብላት ወዮታ ያስከትላል" በማለት ጤፉን የሚገዛው ያጣ የጤፍ ነጋዴ መስሎ ቀረበ:: ኦርቶዶክሳውያን አበው፥ እንደ ፓስተር ዳዊትና ደፍተራ ገለፈት ስለ ክርስትና ገና ያልገባው ይቅርና፥ ባንድምታ ጉባዔያቸው ቆይቻለሁ የሚለውንም እንኳ፥ ከሊቃውንት ጋራ ጊዜ በማሰለፍ የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢር ካላደላደለ በቀር፥ መንፈስ ቅዱስ ላከኝ እያለ ልስበክ የሚለውን ሁሉ ወደሕዝብ እንዲቀርብ የማይፈቅዱት በዚህ አይነት ስሕተት ሰው ይዘው እንዳይወድቁ ነበር::

"ነጭ እንጀራ እያለ ቅጠል የምትበሉ ወዮላችሁ" እያሉ ስለምግብና ስለሆድ የሚሰብኩ፥ ከራሳቸው ጀምሮ ያካባቢያቸው ሰው የሚፈጽመው በደል ሳይታያቸው፥ ከነሱ ርቀው ያሉትን ገዳማውያን አባቶችን ነጭ እንጀራ ባለመብላታቸው የሚዘልፉ ሰባኪወች፥ "ሆድ ለምግብ ምግብም ለሆድ ነው ሁለቱም የሚጠፉ ናቸው" እንደተባለው፥ ዘግይቶ ከሚጠፋው ሆድ በፊት፥ ከስምንት ሰአት በኋል ከሆድ ተለይቶ ከሚጠፋው ምግብ ጋራ አብረው የሚጠፉ ናቸው::

ፓስተር ዳዊት የጨበጠው መጽሐፍ ቅዱስ "ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን፥ ግን መከራ ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጅ አይፈር"(፩ኛ ጴጥ ፬፡፲፭-፲፮) የሚለውን ቢረዳ ኖሮ፥ ስንት፥ ነፍሰ ገዳዮች፥ ሌቦች፥ ዘራፊዎችና ህዝብ አስለቃሾች በአገሪቱ ሞልተው እፊቱ እያሉለት መርጠው በያዙት በተቀደሰው ኑሯቸው በፈጣሪያቸው ፍጹም እምነት ያላቸውን ገዳማውያን ለማዋረድ ባልሞከረም ነበር:: በነሱ ላይ ለሰነዘረው ሰይጣናዊ ፍርዱም፥ ክርስቶስን ምስክር አድርጎ በጎኑ ሊአቆመው ባልደፈረም ነበር::

እንግዲህ የፓስተር ዳዊትን ሁለንተና ስንመረምረው ከሚናገረው አማረኛና ከቆዳው ቀለም በቀር ከሌላ ዓለም የመጣ፥ ስለ ገዳማትና ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምንም ግንዛቤ የሌለው ሰው ነው:: ለመብላት ለመጠጣት ለመወፈር ለመስባት "ጌታ ይበቃኛል" ማለት ከጠቅላላው ክርስቲያናዊ ግንዛቤ የራቀ ነው:: በክርስትና ጌታን የሥጋዊ ስሜት ተበባሪ ማድረግ የኃጢአት-ኃጢአት እንጅ ክርስትና አለመሆኑንም የተረዳ አይደለም:: ይህን አይነቱ ክርስትና በገዳማዊው ክርስትና ላይ ለመፍረድ መንፈሳዊ

ችሎታ ሊኖረው ቀርቶ፥ ከሰባዊ ማስተዋል ጉድለትና ከኃጢአት ባርነት ያልተላቀቀ ነው:: በክርስቶስ ነጻ መውጣት ማለት፥ የሥጋን ፈቃድ በነፍሱ ላይ እንዲሰለጥን መፍቀድና፥ "ጤፍ እንጀራ እያለ ቅጠል የሚበሉ ወዮላቸው" ብሎ በመንፈሳውያን አባቶች ላይ ወዮታ ማወጅ አይደለም::

ሐዋርያት "መጠውኒ የማኖሙ ምስለ በርናባስ ከመ ንሳተፍ ምህሮ አሕዛብ" (ገላ ፪፡፱) እንዳሉት፥ የክርስትና አደራ፥ ለድሆች ሰዎች ቅድሚያ መስጠት ለምግባረ ሠናይ ነበር:: በገዳም ያሉትን አባቶች የሚያሳዝናቸው ጤፍ እንጀራ ሳለ ቅጠል መብላታቸው ሳይሆን፥ ሕዝበ ክርስቲያኑ በረሐብ አለንጋ እየተገረፈ፥ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለራስ ዝና የለድንጋይ ሐውልት አሰርቶ መመረቅ ይቅርና የሆድ አምላኪነት መንፈስ ወሮን፥ ከጾም ከማክፈል ከጸሎት በመራቃችን ወዮልን ወዮታ አለብን አለማለታችን ነው:: ይህን የምለው ፓስተር ዳዊት የሚጓዝበት መንገድና የተሳሳተ ግንዛቤው ከኛ ግንዛቤ ጋር የማይገናኝ እንደሆነ ለማሳየት እንጅ፥ ውፍረቱን እንደ ጸጋ ከቆጠረው ለሱ ይሁነው! ከማለት አልፌ፥ በሰውነቱ ውፍረት እሱንም ሆነ ማንንም መተቼት ክርስትና የሚቀበለው አይደለም::

ፓስተር ዳዊት ይህን ሳይረዳ መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር መሰለፉ፥ ራሷ ክርስትና በፈተና ላይ እንዳለች ያሳያል:: መርጠው፥ ቆርጠውና ወስነው እንስሳትን አስጨንቆና አርዶ ከመብላት ርቀው፥ በዚህ መስመር ተሰማርተው የሚጓዙትን አበው እንደምሳሌ ከመከተል ይልቅ፥ እንብላ እንጠጣ እንጥገብ እንርካ የሚል ስብከት ለማሰራጨት ምግብን ርእስ አድርጎ፥ ማንንም መንቀፍ በቅዱስ መጽሐፍ የተነቀፈና የተከለከለ ነው:: ፓስተር ዳዊት "ምግብ ለሆድ ነው:: ሆድም ለምግብ ነው ሁለቱም ይጠፋሉ" በተባለው ላይ ስብከቱን መሠረት አድርጎ ያሰራጨው፥ ከሱ ጋር ለሚጠፉት ሰዎች የተዘጋጀ ወጥመድ ነው:: ፓስተር ዳዊት "የነጭ ጤፍ እንጀራ እያለ ቅጠል የሚበሉ ወዮላቸው" እያለ በቅዱሳን ገዳማውያን አበው ላይ የሰነዘረውን የተሳሳተ ነቀፋና ትችት ከክርስትና ውጭ እንደሆነ ለማሳየት የጀመርኩትን ለጊዜው ከዚህ ላይ ገትቼ፥ እመቤታችን "እሱን ስሙት" ብላ የተናገረችውን አስመልክቶ ወደተናገረው ትችቱ እሻገራለሁ::

# ፩ኛ. "እሱን ስሙት ብላለች"

<u>ፓስተር ዳዊት ስለምልጃ አንስቶ፥ እመቤታችን ቅድስት ማርያም "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" (ዮሐ ፪: ቁ. ፭) ያለችውን "እሱን ስሙት ብላለች" በሎ ያለቦታው በመጥቀስ ተችቶናል:: ስለምግብ መጽሐፍ ቅዱሱን ያየበትና የተረጎመበት መነጸሩ ከኛ የተለየ እንደሆነ ሁሉ፥ የክርስቶስን ምልጃ ከፍጡራን ከጻድቃንና ከሰማእታት ምልጃ ጋራ በመቀላቀል እኛ ከምንገልጽበት መንገድ በራቀና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተጋጨው፥ በራሱ መንገድ አቅርቦታል</u>:: እራሱ ጌታችን "ስለ እናንተ እንድለምን የምላችሁ አይምሰላችሁ" (ዮሐ ፲፮፡፳፫) ባለው መሠረት ክርስቶስ የማማለድ ተግባሩን በመስቀል ፈጽሞ፥ "በኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ይሠራል" (የሐ ፲፬፡፲፪) ብሎ የማማለድን ተግባር ለቅዱሳን ከከፈተልን በኋላ፥

“ማናቸውንም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እኔ አደርገዋለሁ” (፲፬፡፲፫-፲፬) ብሎ ራሱ ባስተማረን መሠረት፥ ክርስቶስ ያደርግልናል ብለን በማመን አንዳችን ላንዳችን እንማልዳለን:: ጌታችን በሥጋ ከኛ ከመለየቱ በፊት እስከ መስቀሉ ድረስ በተዋሕዶ ድምጹ “አባቴ ይቅር በላቸው” እያለ ሁሉን ነገር ከፈጸመ በኋላ ባማላጅነት ደረጃ አናስቀምጠውም:: በሥጋ ባሕርይ ድካም ተሸንፎ ከክርስቶስ ጸጋ የወደቀ ክርስቲያን፥ በጠፋው ድሪም ምሳሌ እንደገለጸው ወደ ነበረበት ጸጋ የሚመለሰው በንስሐ ነው:: (ሉቃ ፲፭፡፱.፲) በክርስቶስ አምነናል ብለን ከገባን በኋላ ሕሊናችን በሚወቅሰን ኃጢአት ክርስቶስ የማልድልኛል የምንል ከሆነ፥ አንድ ጊዜ ተዋርዶ ሞትን አሸንፎ በኃይልና በግርማ ለፍርድ የሚመለሰውን ክርስቶስን ከመስቀሉ በፊት ወደነበረበት መመለስ ነው (ገላ ፪፡፲፯)::

ይህን መሠረት በማድረግ የኦርቶድክስ ሊቃውንት አበው እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ “ወርደቱ እመስቀሉ ውስተ ሲኦል ወፈትሐ እለ ሀለዉ ህየ ጻድቃነ ሙቁሐነ በኃጢአተ አዳም አቡሆሙ ወአንሥአነ በጽድቀ ትንሣኤሁ እምነ ሙታን ወአርጎወ ለነ ኆኅተ ንስሐ” (ሃይ ፴፯፡፴):: ማለትም፥ “ከመስቀሉ ወደሲኦል በመውረዱ አዳነን:: በአባታችን በአዳም በደል በሲኦል ተግዘው የነበሩትን ፈታቸው:: በእውነተኛ ትንሣኤውም አስነሳን የንስሐ በርም ከፈተልን” በማለት ክርስቶስ እስከ መስቀሉ ድረስ በአማልጅነቱ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ይስማማበታል:: ይህንንም ምሳሌነት በመጠቀም ክርስቶስን የሚከተሉ ሁሉ የአገር ርቀት ሳይወስናቸው በዚህ ዓለም በአካለ ሥጋ እያሉ አንዳቸው ላንዳቸው ይማልዳሉ:: ይህ እምነትና ትምህርት ከክርስቶስ ጀምሮ በጥንት አብያተ ክርስቲያናትም ዘንድ የነበረና ያለ፥ ክርስቶስም እስኪመለስ ድረስ የሚኖር ነው::

“ሰው ነፍሱ በሞት ከሥጋው ከተለየ በኋላ ማማለድ አይችልም” በማለት ከኛ የተለየ አሳብ ያላቸው አሉ:: አባባላቸውን ባንቀበለውም፥ የተጠሩበትና ተስማምተው የሚከተሉት የራሳቸው ግንዛቤ ስለሆነ ልንነቅፋቸው አይገባንም:: የኛ ቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑት ምሥራቃውያን የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ግን፥ “እኔ የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ:: የህያዋን እንጅ የሙታን አምላክ አይደለሁም” (ማቴ ፳፪፡ ፴) ነፍሳት መንፈሳውያን ናቸውና አይሞቱም:: ምልጃ መንፈሳዊ ነውና፥ በማትሞተው ነፍስና በፈጣሪ መካከል ያለ ስለሆነ ከለበስነው ሥጋ ጋራ ወደ መቃብር አይሄድም:: ምልጃን ከማትሞተው ነፍስ አላቆ ከሚሞተው ሥጋ አጣብቆ በመቃብር መወሰን ልክ አይደለም:: የምልጃ ፈቃድ ከላይ ስለምግብ በተገለጸው እንደተረዳነው ከእንስሳት ጋራ ከምንጋራባቸው ሥጋውያን ጠባዮቻችን የተለየ መንፈሳዊ ጠባይ ነው::

ሥጋዊ ኑሮ የእንስሳት ጠባይ የሚጋራው ድንግዝግዝታ ኑሮ ነው:: ከሥጋ መላቀቅ ደግሞ ሙሉ እውቀት እንደሚሰጥ ቅዱስ ጳውሎስ “ዛሬ በመስታወት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፥ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፥ ዛሬስ ከእውቀት ከፍየ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን፥ እኔ ደግሞ እንደታወኩ አውቃለሁ” (፩ኛ ቆሮ ፲፫፡፲፪) ብሏል:: በሥጋ ባሕርይ ድንግዝግዝ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች፥ በሥጋ ድንግዝግዝ ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖች ጸሎትና ምልጃ የሚጠይቁ ከሆነ፥ እንኳን የመለኮት ማደሪያ ለነበረችው ድንግል ማርያም፥ ከዚህ ድንግዝግዝታ ተላቀው በሙሉ መንፈሳዊነት ውስጥ ያሉትን ቅዱሳን

አያማላዱም ማለት ከክርስትና ውጭ ነው:: ይህንንም ብለን በማመናችን ማንም ሊነቅፈን አይችልም:: አይገባውምም::

በክርስቶስና በቅዱሳን ምልጃ መካከል ስላለው ልዩነት በፓስተር ዳዊት የተነገረው ብቻ አይደለም:: ዛሬ በቤታችን ከእያንዳንዱ ሰባኪ የሚሰማው ሁሉ በጉባዔ ከተማርነው ጋር የሚጋጭ ነው:: እግዚአብሔር ቢፈቅድ በርእሱ እመለሰብታለሁ:: ስለ እመቤታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንና መላው ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ከሮማ ካቶሊኮች የምንለያየበት በገለጽኩበት፥ እግር መንገዴንም ከፕሮቴስታንቶችም እንዴት እንደምንለይ የገለጽኩበትን "ቅድስተ ቅዱሳን" በሚል ርዕስ ያቀረብኩትን ጦማር http://www.medhanialemeotcks.org/pdf/Mary_the_Mother_of_Jesus.pdf ይመልከቱ:: ለአንዳንድ የሚያሳስቱ ጥቅሶችን የሚያብራራ ተከታዩን ጦማር እዚህ ላይ ተጭነው ያንብቡ::

የፓስተር ዳዊት የማማለድ ግንዛቤ፥ እንደምግቡ በሥጋ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው:: የሥጋ ፈቃዳችን ከመሬታዊ ጠባያችን ጋራ የሚያያይዘንና ከእንስሳት ባሕርይ ጋራ አንድ የሚያደርገን መብላት መጠጣት፥ ሩካቤ ሥጋና የመሳሰሉት የሥጋ ፈቃዶች ናቸው:: እነዚህን የሥጋ ፈቃዶች ከክርስትና ትእዛዝ ውጭ ከተጠቀምናቸው ነፍሳችንን ለፍርድ የሚያቀርቡ ቢሆኑም፥ ከሥጋ ጋራ በመቃብር ይቆማሉ እንጅ ከነፍስ ጋር አይቀጥሉም:: የመንፈስ ሥራ ግን ከማትሞተው ከነፍስ ጋራ የተያያዘ በመሆኑ፥ ነፍስ በዚህ ዓለም በተሸከመችው ሥጋ ሳለች፥ ነቅታና ተግታ በምልጃ ሥራ ተጠምዳ ከቆየች፥ ከለበሰችው ሥጋ ስትላቀቅ የማማለድ ባሕርይዋ ይቀየራል ማለት፥ የምልጃ ፈቃዷ በሥጋዋ የተወሰነ ነው ማለት ይሆናል::

ባንድ በኩል ሰው በደመ ነፍስ ከሚንቀሳቀሱ እንስሳት የተለየ ነፍስ (ሕይወት) አለችው:: ሲሞት ግን ከሥጋ ተለይታ ወደፈጣሪዋ ትሄዳለች እየተባለ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ምልጃ ከመቃብር ወዲያ አይሻገርም ማለት፥ በጥንት አብያተ ክርስቲያናት ግንዛቤ እርስ በርሱስለሚጋጭ ተቀባይነት የለውም:: ይህ አባባል "ሰው የሚንቀሳቀሰው እንደ እንስሳ በደመ ነፍስ ነው፥ በውስጡ የተለየ ነፍስ የለውም:: ሁሉም በመቃብር ተካቶ ይቆያል" የሚለውን የጀሆቫ ዊትነሶችን አባባል ካልተቀበሉ በቀር፥ ሥጋ የለበሰች ነፍስ ማማለዷን እያመኑ ከሥጋዋ ከተለየች ምንም አታውቅም፥ አታማልድም ማለት፥ ማወቅንም መንፈሳዊነትንም ለሚሞተው ሥጋ መስጠት ይሆናል:: ፓስተር ዳዊት ከመቃብር በማያልፉት በሆድና በምግብ ላይ ትምህርቱንና እምነቱን እንደመሠረተ፥ የማማለዱንም ተግባር ከሥጋ ጋራ በማቆራኘት በመቃብር ወስኖታል:: ለራሱ የመረጠውን ቢከተል የሚነቅፈውና የሚተቸው መኖር እንደሌለበት ሁሉ፥ ይህን ያህል በራቀ ግንዛቤው እኛን ለመንቀፍና ለመተቸት እውቀቱም ሞራሉም ብቃቱም ሳይኖረዉ እኛን በመንቀፉ፥ መነቀፍ፥ መገሰጽና መወገዝ የሚገባው ሰው ነው::

ፓስተር ዳዊት ከአፍሪካን አሜሪካውያን በገለበጠው ባሕል፥ ከነሱ ያየት አንዷት እንኳ እንዳትቀረው እስኪአልበው ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ ድረስ ይዘል፥ ይጮህና በመሐረብ ፊቱን ይጠርጋል:: እኔ እንደገመትኩት ከሆነ የፓስተር ዳዊት መልእክት ሁለት ገጽ አለው:: አንደኛው የራሱን ማንነትና በኢትዮጵያ ያሉትን ሰዎች ምንነት ለመደምሰስ ሲሆን፥ ሌላው እናንተን መስየ እናንተን አሀየ እንደምታዩኝ እንደናንተ ልቤ እስኪፈነዳ እየሰበኩ ነውና ገንዘብ ላኩልኝ የሚል መልእክት፥ ለቀዳቸው (ኮፒ) ላደረጋቸው ቡድኖች የእርዱኝ መልእክቱን ለማስተላለፍ እቅድ ያለው ይመስላል::

አፍሪካን አሜሪካውያን ወገኖቻችን፥ በባሕል በቋንቋና በነገረ መለኮት አተረጓጎማችን ከኛ ቢለዩም፥ ብዙ ያዩ በብዙም የተፈተኑ፥ የባህልና የታሪክ መዘረፍ ምን ያህል ከባድ መሆኑን ከኛ የበለጠ ስለሚያውቁት፥ ለተቀደሰው ለገዳማዊው ባህል ይቅርና፥ ለማነኛውም ባሕልና ታሪክ እጅግ የሚጠነቀቁ መሆናቸውን አውቃለሁ:: ጥንቃቄያቸውንም አሜሪካ መጥተው በተለያዩ መስኮች ተሰማርተው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም እኔ ከማውቀው የበለጠ እንደሚአውቁ አምናለሁ:: በአገራችን ገብቶ የሚተራመሰው ሁሉ ድርጅት እትብቱ የተሳሰረበት የውጭ ድርጅት ስላለው፥ ፓስተር ዳዊትን ወደ ኢትዮጵያ የላከው ሞግዚት የትኛው ድርጅት እንደሆነ ብናውቀው፥ ፓስተር ዳዊት የሚፈጽመውን መረን የለቀቀ ዘርቅ ቢገለጽላቸው፥ ክርስትና ሁሉም በተጠራበት መንገድ ቢቀጥል የሚፈቅድ መሆኑን የሚረዱ የእምነትና የሞራል ሰዎች ከሆኑ ፓስተር ዳዊትን ይገስጹታል እንጅ በሞግዚትነታቸው እንደማይቀጥሉ እርግጠኛ ነኝ::

ማንም ቢሆን ራሱ ባልተረዳው ነገር ሌላውን መዝለፍ እራስን ማዋረድ ነው:: ፓስተር ዳዊት በኛ ላይ በሰነዘረው ዘለፋ ሲለካ፥ "እሱን ስሙት" ያለችውን የእመቤታችንን ትእዛዝ የተረዳ አይደለም:: መንፈሳዊ ስሜትም የለውም:: እመቤታችን "እሱን ስሙት" ያለችውን እራሱ ቢሰማና ቢረዳ ኖሮ፥ ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የምታስተምረውን ነገረ መለኮት ከመንቀፍና በውስጧ እያገለገሉ ያለፉትን ሊቃውንት አበው ከመዝለፍ ይልቅ፥ እራሷ እመቤታችን "ትቢተኞች ተዋርደው እንደሚበተኑ፥ ገዥዎችም ከዙፋናቸው በሀፍረትና በቅሌት እንደሚወርዱ፥ በገዥዎች የተዋረዱትም ከፍ እንደሚሉ፥ በገዥወች ሥርአት የተራቡት እንደሚጠግቡ፥ ከሕዝቡ በዘረፉት ወርቅና ብር የተሞላው የበዝባዝ ገዝወች እጆችን ባዶ እንደሚሆኑ" (ሉቃ ፩፡፶፩-፶፫) ያወጀችውን፥ በውስጧ ተሰልፈው አገርን በመበደል፥ ሕዝብን በመዝረፍ ላይ ላሉት ግብራቸውን ከነስማቸው እየጠቀሰ ይነግራቸው ነበር:: በግብራቸው በጠባያቸው ተነቅፈው ቤተ ክርስቲያንን የሚያስነቅፉ፥ በክርስቶስ ልደትና ትንሳኤ በዓል እያሳበቡ የኬክ ገጸ በረከት ካላቀረባችሁ እያሉ፥ በደብር አለቆች ላይ የአይነ ቁራኛ ፖሊሲ የዘረጉ፥ የራሳቸው ሲኖዶስ የነቀፏቸው፥ ሕዝበ ክርስቲያን የከሰሳቸው ስለሆኑ በዚሁ በእመቤታችን አዋጅ አቡነ ጳውሎስን ቢገስጽ፥ "ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡ እንጅ አትተባበሩ "(፩ኛ ቆሮ ፭፡፲፫) የሚለው ትእዛዝም ስለሚደግፈው፥ ለምን አልክ፥ ብሎ ከቤተ ክርስቲያናችን አካል ሊቃወመው የሚችል አንድም ሰው አልነበረም:: እነዚህን ሁሉ ተራምዶ "ነጭ ጤፍ አልበሉምና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገቡም" እያለ የአቡነ ጳውሎስን አመራር ተጸይፈውና ርቀው ያሉትን ገዳማውያን አበውን ለመዝለፍ "እሱን ስሙት" ያላቸውን የእመቤታችን አዋጅ መጠቀሙ የደፍተራ ገለፈት ታናሽ ወንድም አድርጎ ራሱን አቅርቧል::

ከነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጀምሮ ዛሬ በገዳም ያሉት፥ ፓስተር ዳዊት የፈረደባቸው ቅዱሳን አበው፥ "ይኄይስ ብእሲ ዘበሐማሩ ይትቀነይ ሎቱ፡ እምነ ዘከብረ ያነብር ሎቱ ወይትፈአም ኅብስተ" ( መጽሐፈ ምሳሌ ፲፪፡፱) የሚለውን፥ ማለትም፥ በአድር ባይነት ሆዱ፥ እውነትንና ሕሊናውን ሰርዞ የራሱን ሰባዊ ክብሩን ከካደ፥ እየተራበ እየተጠማ ክብሩን የጠበቀ ድሀ ሰው ይሻላል፡ እያሉ የመንፈስ የልዕለ አዕምሮ አዕማድና ምንጮቻችን ናቸው:: "በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑ ምሳሌ ሁኑ እንጅ ማንም ታናሽነትሕን አይናቀው" (፩ኛ ጢሞ ፬፡፲፪) ተብለን በታዘዝነው መሠረት፥ ከመስመር በወጣ ማስረጃ በሌለው ግላዊና ድርጅታዊ ጥላቻ ቅዱሳን ምሳሌዎቻችንን ይቅርና፥ ማንም

ቢሆን ሲዘለፍና ሲነቀፍ እየሰማንና እያየን፥ በዝምታና በትዝብት እንድናልፍ ኢትዮጵያዊ ስሜታችን አይፈቅድልንም:: ይህ ስሜት ከድርጅት ክልል የሰፋ ሞራል ስለሆነ፥ በፓስተር ዳዊት ዙሪያ ካሉት ከፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ወገኖቻችን ሕሊና ውስጥም ሊኖር የሚገባ ነው::

ነፍሳቸውን ይማርና ክቡር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ያንቀላፋውን አዕምሮ ቀስቅሶ ግራና ቀኝ እንዲያይ በሚያዘጋጅ ድምጻቸው "ሁሉንም ለይቼ አይቼዋለሁ" ብለው የተቀኙትን የሞራል ውርስ እዚህ ላይ ብጠቅሰው ተገቢ ይመስለኛል:: መሰደዳችን የተሰደድንበተን አገር ምግብ እየበላን ሆዳችንን እየሞላን ለመኖር ብቻ አይደለም:: ሌላውን ለመተቸትም፥ ለመንቀፍም ሆነ የኛን አውልቀን ጥለን ከሌላው መቀበል የምንችለው፥ የአዕምሮ ብስለታችን ከተቀበለን ኅብረተ ሰብ የምንለይበትንና የምንመሳሰልበትን ባሕልና ዘይቤ ለይቶ ከመረዳት ደረጃ ላይ ሲደርስልን ብቻ ነው::

ስሜቱን ከዓለማዊ ምኞት ያልገታ፥ ዘመኑ ባፈራው ቅንጦት ቤት ውስጥ በመኖር፥ በፈረንሳይ ሽቶ፥ በሩቅ ምሥራቅ ሥጋጃ በመሽሞንሞን ላይ ሆኖ በገዳማውያን አበው ላይ ነቀፋ የሚሰነዝረውን ፓስተር ዳዊትን፥ ሚዛናቸውን የጠበቁ ኢትዮጵያውያን ወገኖች በስሜ ይመጣሉ ከተባሉት አንዱ መሆኑን ይረዱታል:: "የመንግሥተ ሰማይ በር ዋሻ መሰላቸው?" እያለ ፓስተር ዳዊት የዘመተባቸው ቅዱሳን አባቶች፥ "ሕዝቤ ከእውቀት ጉድለት የተነሳ ጠፋ" ብሎ ሆሴዕ እንዳለቀሰላቸው ሰዎች፥ በአዕምሮ ጎደሎነቱ፥ በገዳም ያሉ አባቶች የሚያለቅሱለት እንደሆነ መረዳት አያቅታቸውም::

የፓስተር ዳዊት ክርስቲያናዊ አገላለጽ ዘይቤ (term) ከኛ ከኦርቶዶክሳውያን አገላለጽ ጋራ የማይገናኝ ከመንፈሳዊነት የራቀ ዓለማዊ አገላለጽ ነው:: ለምሳሌ፡- መቀበል የሚለውን ቃል፥ "እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ" የሚለውንና "ለተቀበሉኝ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው" የሚለውን በከተማ ጮሌነት ከሚያቀርበው ይልቅ፥ ባማረኛው ለዛና በባሕሉ ጥልቀት ያደጉት የገጠር ወገኖቻችን አሳምረው ያቀርቡታል:: ክርስቲያናዊ አገላለጽ ዘይቤያችንን (term) ከውጭ በቀላወጠው መንገድ ማቅረብ የሱን ዝቅተኝነት የሚያሳይ ነው::

<u>አብ አጽንቶ፥ መንፈስ ቀድሶ ያዘጋጃትን የእመቤታችንን አጸናነስ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት በተናገሩበት አንቀጽ ሁሉ "ሰማይና ምድር ሊቀበሉት የማይችሉትን" እንዴት ቻልሽው?</u> እያሉ በገለጹባቸው ዘይቤዎች (terms) መቀበል የሚለውን ቃል እንጠቀማለን:: <u>ይህ ልንተችበት የማይገባ የመላ ምሥራቃውያንና የኛም ያገላለጻችን መንገድ ነው:: ከግል ጸሎታችን እስከ ማህበር ጸሎታችን (ቅዳሴያችን) የምንገልጸው የተቀበልከን፥ ያቀረብከን፥ ያቀፈን፥ የተሸከመን፥ ታጋሹና ከሀሊው እግዚአብሔር እያልን ነው:: የጸሎት መደምደሚያችን፥ ተጣልተን መታረቂያችን እግዚአብሔር ይቀበለው ነው</u>::

<u>እነ ፓስተር ዳዊት የነቀፏቸውን ገዳማውያን አባቶችና እናቶች ወደ ገዳም ሄደው ክርስቶስን ተቀብላችኋል ድናችኋል? ብለው ቢጠይቋቸው፥ "በመጠን ኑሩ ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና፥ በዓለም ያሉትን ወንድሞቻችሁን ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት"( ፩ኛ ጴጥሮ ፭፡፰) እያለ ቅዱስ ጴጥሮስ የተናገረውን ተረዱት፡ ለሚሰሟችሁም አካፍሉት:: እኛም በገዳም ያለን ከዚህ ዓይነቱ አውሬ ለመሸሽ ነው</u>

ከማለት በቀር፥ ስለራሳቸው መዳንና አለመዳን የሚመልሱት "መድኃኔ ዓለም ያውቃል" ብለው ነው:: እኔንም ቢጠይቁኝ የምመልስላቸው ይህንኑ ነው::

ገንዘብ ለመሰብሰብ ሲል "እኔ ክርስቶስን ተቀብያለሁ" ብሎ ባፉ እየተናገረ በግብሩ ክርስቶስን ክዶ እየተጋለጠ ባደባባይ ራቁቱን የቆመው የፓስተር ዳዊት ቢጤ ቁጥር ብዛት በዓለም ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ የሚዘለቅ አይደለም:: ጌታችን ባፋቸው "ጌታ ጌታ" እያሉ በንግግራቸውና በግብራቸው ክርስትናን የሚክዱትን እንደ ፓስተር ዳዊት ያሉትን አስመሳይ ፎካሪዎች፥ ቅዱስ ጳውሎስ "ለበጎ ሥራ የማይበቁ በሥራቸው እግዚአብሔርን የሚክዱ ናቸው"(ቲቶ ፩:፲፮) እያለ በግልጽ ለይቶ አስቀምጧቸዋል:: አሁን ከቤተ መቅደሳችን ውስጥ ወደመነጨው ፈታና እሻገራለሁ::

# ለ. በዘመናችን ቤተ ክርስቲያናችንን ከውስጥ የገጠማት ፈተና

ደፍተራ ገለፈት ጠልስሞ ያቀረበው፥ ከሦስቱ እጅ አንዱ ነፍሳቸውን ይማርና ከብጹዕ አቡነ ማቴዎስ የተወሰደ ነው:: ከሶስቱ እጅ ሁለቱ ነገረ መለኮት ተማርኩ ካለበት ከአየር ላንድ የተገለበጡ ናቸው:: ሁለቱም ማለትም፥ ፓስተር ዳዊትና ደፍተራ ገለፈት የተነሱባቸውና የመጡባቸው አቅጣጫወች የተለያዩ ቢሆኑም፥ ኃይላቸውን አጎዳኝተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከኢትዮጵያውያን ልቡና ለመንቀል፥ በሃይማኖት አባቶቻችን በነቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና በጎርጎርዮስ ዘስኑይ ላይ ምሕረተ አብ እንዳለው ጂሐድ ያወጁ ናቸው::

ያሳደጉት አቡነ ማቴዎስ በደብረ ሊባኖስ ሊቃውንት ተወግዘው በምትካቸው ጳባጤ ክፍለ ዮሐንስ የተሰየሙበት ምክንያት በ፱ኝ መለኮት እምነታቸው ነበር:: የተዋሕዶ ሊቃውንት አበው ጠልሰሚን አቃጥለው እሳቸውን ከገዳሙ እንዲወጡ የታገሏቸው፥ ይህን ክህደት በገዳሙ ዙሪያ ለሌላ እንዳያሰራጩት ነበር:: ይሁን እንጅ ጠልሰሚ በአቡነ ማቴዎስ ጭንቅላት የነበረውን ተሸከመች እንጅ፥ ምንጯ የአቡነ ማቴዎስ ጭንቅላት ስለነበር፥ ለደፍተራ ገለፈት አውርሰውታል:: የደብረ ሊባኖስ ሊቃውንት አባቶቻችን ካቃጠሉት የአቡነ ማቴዎስ ጠልሰም ከያዘው የዘጠኝ መለኮቶች ክህደት ይልቅ እያስተማሩ ያሳደጉት ልጃቸው ደፍተራ ገለፈት "ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት" በሚል ያዘጋጀት ጠልሰም በውስጡ የተሸከመችው የክህደት ብዛትና አይነት እጅግ የከፋና የሰፋ በመሆኑ ይታረማል ተብሎ የሚገመት አይደለም::

የደፍተራ ገለፈትን ኑፋቄና በደል ከአቡነ ማቴዎስ እጅግ የከፋ የሚያደርገው፥ አቡነ ማቴዎስ ሥላሴ በመለኮት፥ በስልጣንና በባሕርይ አንድ፥ የሚለውን ሠርዘው፥ በስም በአካልና በግብር ያላቸውን ሶስትነት

በሶስት አባዝተው ዘጠኝ መለኮት የሚለውን ብቻ ሰበኩ እንጅ፥ እመቤታችን በማዳኑ ሥራ ተባበረች አላሉም።

- እንደ ደፍተራ ገለፈት ስለ ስላሴ አንድነትና ሶስትነት ባስተማሩት ሊቃውንት አበው ላይ አልዘመቱም።
- መጻሕፍቶቻቸውም ስሕተት አለባቸው የሚል የድፍረት ቃልም አልሰነዘሩም።
- ስለ አገራቸው፥ ስለቤተ ክርስቲያናቸውና ስለተዋሕዶ ሃይማኖታቸው እየታገሉ ያለፉ አባቶቻችን ታሪክንም ለመደምሰስ አልሞከሩም።
- ቤተ ክርስቲያችናችንን ከአቻወቿ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ገንጥለው በመለየት ወደ ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንግባ አላሉም።

በዚያው ባንዲ ስሕተታቸውም ቢሆን እንኳ በሞት ይህችን ዓለም ለቀው ወደፈጣሪያቸው ከመሄዳቸው በፊት ተጸጽተውበት ሊሆን ይችላል። እኔ አቡነ ማቴዎስን የጠቀስኳቸው፥ እሳቸውን ለመክሰስና ለመንቀፍ ሳይሆን፥ ያሳደጉት ልጃቸው የተወገዙበትን ስሕተት ከራሱ ብዙ አይነት ክህደቶቹ ጋራ አቆራኝቶ በጠለሰመው ጠልሰሙ ላይ ፎቷቸውን ለጠፎ ለሳቸው መታሰቢያ አርጎ ስላቀረበው ነው።

ያስተማሩኝና በምሳሌነት የምጠቅሳቸው የደብረ ሊባኖስ ሊቃውንት አባቶች በዘመናቸው የገጠማቸውን የአቡነ ማቴዎስን ጠልሰም ምንጩን እየጠቀሱ እንዳቃጠሉት፥ እኔም የነሱን ምሳሌነት በመከተል በዘመኔ የገጠመኝን የደፍተራ ገለፈትን ጠልሰም ሰብስቤ ለማቃጠል እድሉ ባይገጥመኝም፥ አከታትየ በማቀርባቸው ጦማሮች ምንጩን እየጠቀስኩ ሳልመሰክር ብቀር ከሚያስከትልብኝ ሕሊና ወቀሳ ለማምለጥ ብቻ እንጅ ሙት ወቃሽ ለመሆን ፈልጌ አይደለም። ለምን ስማቸውን ጠቀሰ ብሎ በእኔ ቅር የሚለው ካለ፥ ወቀሳውን ቅሬታውን መቀበል ያለበት፥ ይህን ያህል የተዘርከረከና የከፋ ክህደት በተብተበበት ጠልሰሙ ላይ ፎቶ ግራፋቸውን ለጥፎ ያቀረበው ደፍተራ ገለፈት ነው። ከዚያም አርመውና እንዲነበብ አርገው ለሕዝብ በአዋጅ ያቀረቡ ተባባሪዎቹ ናቸው እንጅ፥ እኔ ልውቀስ አይገባኝም። አሁን የ፱ መለኮቶችን ትምህርትና እምነት ወዳመነጨው ክህደት እሻገራለሁ።

# ፩ኛ. በአንድነት በሦስትነት የሚኖር አምላክ

ደፍተራ ገለፈት በዚህች ጠልሰም በገጽ 125 ላይ ከአቡነ ማቴዎስ የተማረውን "ከእመቤታን የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ ሳይሆን በአንድነት በሦስትነት የሚኖር ረቂቅ አምላክ መሆኑ ነው" በማለት በደቀመዛሙርቱ (ቢጤዎቹ) በሚገባ መነበብ በሚችልበት ስልት አሳርሞና አስተካክሎ በዋሸንግተን ዲስ ቅድስት ማርያን ርዕሰ አድባራት ቤተ መቅደስ ላይ በገሀድ አወጀው። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነገረ መለኮት፥ ክርስቶስ ከቅድስት ደንግል ማርያም መወለዱንና ረቂቅ አምላክ እንደሆነ ያላንዳች ጥርጥር ይታመናል። መሠረቱም እሱ ነው። ይሁን እንጅ ክርስቶስን ብቻ ለይቶ "በአንድነት በሦስትነት የሚኖር

አምላክ” ብሎ መናገር፥ ከክርስትና ትምህርትና እምነት ውጭ ነው:: ምክንያቱም ከሶስቱ አካላት አንዱን ወልድን ብቻ ለይቶ “በአንድነት በሦስትነት የሚኖር አምላክ” ከተባለ፥ አብንም ለይቶ በአንድነት በሦስትነት የሚኖር አምላክ ከተባለ፥ መንፈስ ቅዱስንም ለይቶ በአንድነት በሦስትነት የሚኖር አምላክ ከተባለ፥ አንዱን አካል ሶስት አካላት አድርጎ ያቀረበ፥ 3 ን በ 3 (3x3=9) አባዝቶ ወደ ፱ኝ መለኮት የመራ፥ አቡነ ማቴዎስን ያስወገዛቸው ትምህርትና እምነት ነው:: ስለዚህ ደፍተራ ገለፈት አንዱን አካል በመለየት ”በአንድነት በሦስትነት የሚኖር አምላክ” በማለቱ ለሚያገኛት ገንዘብ ሲል ሐሳቤን ለወጥኩ ሊል ቢችልም፥ የዘጠኝ መለኮቶች አማኝና ሰባኪ አይደለሁም ብሎ እራሱን ሊሸፍን አይችልም:: ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለም፥ በሥላሴ አንድነትና ሶስትነት የሚያምን ሁሉ የማይቀበለው ትልቅ ክህደት፥ ቀድሶ ከማቁረብ ብቻ አይደለም፥ ከምእመንነት እንዲገለል የሚያደርግ ነው::

የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ሊቃውንት አበው ሥላሴ ወይም እግዚአብሔር ካላሉ በቀር አብን ወይም ወልድን ወይም መንፈስ ቅዱስን ለብቻ ጠርተው ባንድንነትና በሶስትነት የሚኖር አምላክ አይሉም:: በአድነትና በሶስትነት የሚኖር አምላክን ለመግለጽ ስላሴ ወይም እግዚአብሔር ብለው ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚለው ስም ላንድነትም ለሶስትነትም ይጠቀሙበታል:: ሊቃውንት አበው የገለጹትን ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች እጠቅሳቸዋለሁ::

- ቅዱስ አትናቴዎስ:- “እስመ ሥጋሁ ለእግዝእነ አኮ እምእግዝእትነ ማርያም ወኢየአምን ይእዜ በሥላሴሁ ለእግዚአብሔር ከመ ውእቱ ፫ቱ አካላት”(ሃ.አበው ም. ፳፱፡ቁ.፲፰) የመለኮትን ውሕደት ለሚጠራጠሩ ሰዎች ባስረዳባት አንቀጹ ስለ ጌታችን መለኮታዊ ባሕርይ ሲገልጽ፥ እግዚአብሔር እያለ እንጅ ክርስቶስ ወይም ኢየሱስ ወይም ቃል ብሎ አይደለም::
- ቅዱስ ባስልዮስም:- “አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር፥ እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እስመ አሐዱ ውእቱ መለኮተ ሥላሴ ወሠለስቲሆሙ አሐዱ እሙንቱ በመለኮት” (ሃ.አበው ም. ፶፯፡ቁ.፯) አለ::
- ቅዱስ ዲዮናስዮስም:- “አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር፥ እብል በእንተ ሥላሴ፡ ወሥላሴሂ አካላት እሙንቱ” (ሃ.አበው ፻፩፡ ቁ.፯) አለ::
- ቅዱስ ዘሱኑትዩም:- “ወሶበሂ ንቤ መለኮት አው እግዚአብሔር ንብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ” (ምዕ ፻፲፡፰) አለ::
- ቅዱስ ሕርያቆስም:- “ወመለኮትሰ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ አሐቲ መንግስት ወአሐቲ ሥልጣን ወአሐቲ ምኩናን” (፻፸፪ ገጽ ቁጥ ፶፯) አለ::
- ቅዱስ ዲዮስቆሮስም:- እግዚአብሔር በመለኮቱ፥ እግዚአብሔር በትስልቱ፥ እግዚአብሔር በመንግሥቱ፥ ነበረ፥ (ቅዳሴ ዲዮ ገጽ ፫፻፶፱ ከቁ ፫ እስከ ፰) አለ::

ስለ ክርስቶስ ሲናገሩ “እስመ በጽድቅ ተሰፋነ በአሐዱ አካል እም አካላቲሆሙ” (፲፡፲፰) ወይም ዘእንበለ ዳእሙ ባሕቲቱ” (ሃ.አበው ፲፩፡ቁ.፫) እያሉ ነው:: ከሶስቱ አንዱን ብቻ ነጥሎ “በአንድነት በሦስትነት የሚኖር” የሚል ቢኖር፥ “ናወግዝ ወንረግም ሃይማኖቶሙ ርኩስተ ለሰባልዮሳውያን እለ ይብሉ

እስመ አብ ውእቱ ወልድ ወውእቱ መንፈስ ቅዱስ፥ ወወልድሂ ካዕበ ውእቱ አብ ወውእቱ መንፈስ ቅዱስ፥ወመንፈስ ቅዱስሂ ውእቱ አብ ወውእቱ ወልድ ወይቤሉ አሐዱ ገጽ ዘስሉስ ቅዱስ ወ፫ቱ አስማት"(ሃ.አበው ፲፱፥ቁ.፲፫) ይህም ማለት፡ አብ ወልድ ነው፥ ወልድም መንፈስ ቅዱስ ነው:: ወልድ አብ ነው:: ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው:: መንፈስ ቅዱስ አብም ነው፥ ወልድም ነው:: እያሉ የሚያስተምሩትን አጥብቀን በመቃወም እናወግዛለን እያሉ ሰለስቱ ምዕት ተናግረዋል::

ስለዚህ ይህን አባባል ደፍተራ ገለፈት፥ ሶስትን በሶስት አባዝተው እያስተማሩ ካሳደጉት ካቡነ ማቴዎስ ወስዶታል:: ከአቡነ ማቴዎስ የወሰደው ካልሆነም፥ የአብንና የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና ሰርዞ እየተለዋወጠ የሚመጣው ያው አንዱ አካል ብቻ ነው ብሎ የካደውን በዘመናችን ኢየሱስ ብቻ (only Jesus) እየተባለ የሚሰበከውን፥ የጥንቱን የሰባልዮስን እምነት ነበርኩበት ከሚለው ከአየር ላንድ ትምህት ቤት ቀላውጦታል:: ሌላም ደፍተራ ገለፈትን ከቤተ መቅደስ ብቻ አይደለም ከተራ ምዕመንናት የሚያባርረው ክሕደት በጠልሰሙ ገጽ 121 ላይ "አምላክ በባሕርይ ሰው ሆነ፥ ሰውም በጸጋ አምላክ ሆነ" ብሎ የጠለሰመው ነው::

# ፪ኛ. "አምላክ በባሕርይ ሰው ሆነ፥ ሰውም በጸጋ አምላክ ሆነ" (ገጽ 121)

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንት አበው ስለ ክርስቶስ "አምላክ በባሕርይ ሰው ሆነ፥ሰውም በጸጋ አምላክ ሆነ" የሚለውን እምነትና ትምህርት ያወግዙታል:: በጸጋ የከበርነው ጸጋ የሚመለከተን እኛን ክርስቲያኖችን እንጅ ክርስቶስን አይደለም:: ከእምቤታችን ከፍሎ መለኮት የተወሐደው የክርስቶስ አካል አምላክ የሆነው በተዋሕዶ እንጅ በጸጋ አይደለም:: ከጥንት ጀምሮ እስከኛ ዘመን ያሉ ሊቃውንት አበው የደፍተራ ገለፈትን እምነትና ትምህርት ያወግዙታል::

- "ነሣእነ ንሕነ ኲልነ ጸጋ ህየንተ ጸጋ በዲበ ጸጋ እስመ ኦሪት በሙሴ ተውሕበት ለነ ወጸጋሰ ወጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ኮነ ለነ"( ዮሐ ፩፥፲፯):: እኛ ሁላችን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጠን:: በሙሴ ኦሪት ተሰጠች:: ጽድቅና ጸጋ ግን በጌታችን በኢየሱስስ ክርስቶስ ተሰጠን:: ይላል ወንጌሉ::
- ቅዱስ ጳውሎስም ወንጌሉን መሠረት አድርጎ በሮሜ መልእክቱ ላይ "ወጽድቅሰ በከንቱ ኮነ በጸጋ ዚያሁ ረከቡ ሕይወተ በኢየሱስ ክርስቶስ" (ሮሜ ፫፥፳፬) "እስመ ተግባራሰ ሊኃጢአት ወረባሃ ዚአሃ ሞት፥ ወጸጋ እግዚአብሔርሰ ሕይወት ዘለዓለም በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ"( ሮሜ ፮፥ ፳፫) አለ:: ማለትም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በተፈጸመው ቤዛነት በጸጋው ይጸድቃሉ:: ይህን የሐዲስ ኪዳኑን ትምህርት መሠረት በማድረግ ሊቃውንት አበው በጸጋ መክበርንና መጽደቅን የሚሰጡት ክርስቶስን ተቀብለው በጸጋው ለሚከብሩና ለሚጸድቁ ክርስቲያኖች እንጅ ለክርስቶስ

አይደለም:: በነዚህና በሌሎችም ብዙ መሠረታውያን ምስክሮች ““አምላክ በባሕርይ ሰው ሆነ፥ ሰውም በጸጋ አምላክ ሆነ” የሚለውን የደፍተራ ገለፈትን ትምህርትና እምነት አጥብቀው ያወግዛሉ::

ለምሳሌ፡-

- አትናቴዎስ “እስመ ኢኮነ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር በጸጋ ከመ ወልደ እጓለ እመሕያው”(፷፫፥፬) “ውእቱ አምላክ ዘበአማን ወአኮ በጸጋ”(ሃ.አበው ፯) “ወይሬስዮ ወልደ በፀጋ ከማነ ውጉዘ ለይኩን ” (ሃ.አበው ፷፫፥፲፯) በማለት ደጋገሞ ተናገረ:: ይህም ማለትም፡- የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተራ ሰው በጸጋ አልከበረም:: ወይም በጸጋ አምላክ ሆነ አይባልም::
- በቃለ ግዝትም “እመቦ ዘይብል እስመ ቃለ እግዚአብሔር ከመ ብእሲ ዕሩቅ ወከመ አሐዱ እምነብያት ነሥአ ፀጋ. . . . በከመ ጽሑፍ ውጉዘ ለይኩን”(ቃለ ግ ምዕ ፻፲፯፥ ክፍ ፲ ቁት ፩) ተባለ:: ማለትም፥ እንደ ነብያት ክርስቶስ በጸጋ ከበረ የሚል ካለ የተወገዘ ይሁን::

ይህ የደፍተራ ገለፈት ትምህርት በታሪካችን ተመዝግቦ እንደምንረዳው፥ ኢትዮጵያውያንን በወንዝ፥ በተራራ፥ በድንበር፥ በቋንቋና በዘር ከፋፍሎ የኢትዮጵያን ህልውና ለመደምሰስ ሙከራ ሲያደርግ በዘመኑ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና ያገሪቱ መሪ እነ አጼ ፋሲል ያባረሩት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ አልፎንሱ ማንዴዝ የተባለው ጠላት የተከለው እሾሕ ነው::

ይህን እሾሕ እንዴት፥ መቼና ለምን በኢትዮጵያ እንደተከለው ነፍሳቸውን ይማርና መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬና አቡነ ጎርጎርዮስ ገልጸውታል:: አልፎንሱ ማንዴዝ በሚባል ሰው እየተመራ ወደ አገራችን የመጣው የሮማ ካቶሊክ ልኡካን ቡድን ነበር:: በዘመኑ የነበሩት ሊቃውንትና የአገሪቱ መሪዎች እነ አጼ ፋሲል እንዲህ ሲሉ በነ ማንዴዝ ላይ ምሬታቸውን ገልጸዋል:: “እንዳልተጠመቅን ቆጥረውን እንደገና እናጥምቃችሁ አሉን:: በእንጨት የተሰራውን የኛን መንበር አቃጥለው የራሳቸውን የድንጋይ መንበር በቤተ መቅደሳችን አቆሙ:: በኛ ቀሳውስት የተባረከውን እንዳልተባረከ በመቁጠር እንደርኩስ ዕቃ በእሳት አቃጠሏቸው:: የተደረገውን ሁሉ በይቅርታ ለማለፍ ስለ ማይቻል ከዚህ በኋላ የሚደረገው ውይት ፍሬ የለውምና ካገራችን ይወጡልን” ብለው ካገር አባረሯቸው:: ማንዴዝ የተባለው ጠላትም፥ በበኩሉ ከኢትዮጵያ ተባሮ ከወጣ በኋላ “በኢትዮጵያ ሁለት እሾህ ተክየባታለሁ” ብሎ ያደረገውን ገለጸ:: ወደፊት ሊፈጽመው አስቦት የነበረውን እቅዱንም “ኢትዮጵያን ወደላቲን ባህል ለመለወጥ አስቀድሞ ሀገሪቱን በጦር ኃይል መያዝ ያስፈልጋል አለዚያ ድካማችን ሁሉ ፍሬ አላስገኘም” ብሎ በዘመኑ የሮማን ካቶሊክ ኃያል መንግሥት ወደነበረው ወደ እስፓኝ ንጉሥ ጻፈ:: አቡነ ጎርጎርዮስ በጻፉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ (54-55) ላይ ተመልከት::

<u>ደፍተራ ገለፈት ከቤተ መቅደሳችን እንዲውጣ ከላይ የተጠቀሰው ታሪካችንና የዘመተበት የተዋህዶ የሃይማኖታችን እየፈረዱበት ነው</u>:: ይህ ፍርድ የመነጨው ከንግግር ስሕተት (ዳህጸ ልሣን) ሳይሆን፥ አጥንቶ አምኖበት፥ አራሚዎቹንም አስተምሮና አሳምኖ አሳትሞ ባቀረበው ጠልሰሙ ማንዴዝ

*"ኢትዮጵያን ወደ ላቲን ባህል ለመለወጥ አስቀድሞ ሀገሪቱን በጦር ኃይል መያዝ ያስፈልጋል አለዚያ ድካማችን ሁሉ ፍሬ አላስገኘም"* ያለውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያላንዳች መወላወል ራሱ በጠልሰሙ አረጋግጦ በገለጸው ነው:: አባቶቻችን፥ ይህን ተንኮልና ደባ የፈጸመውን ማንዴዝ የተባለውን ጠላት ሳይወላውሉ "የተደረገውን ሁሉ በይቅርታ ለማለፍ ስለ ማይቻል ከዚህ በኋላ የሚደረገው ውይይት ፍሬ የለውምና ካገራችን ይወጡልን" ብለው በወሰዱት ሞራላዊ፥ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ርምጃ ነው:: ደፍተራ ገለፈት ከቤተ መቅደሳችን ውጣ የሚባልበት ከዚህ ውጭ በሆነ ምክንያት አለመሆኑን አንባቢ ታዛቢና ያገባኛል የሚል ሁሉ የታሪኩና የሃይማኖቱ አካል ይረዳ ዘንድ፥ የሞራል የሃይማኖትና የታሪክ ግዴታው እንደሆነ መገንዘብ አለበት::

የደፍተራ ገለፈት ክህደትና ስሕተት ተዘርዝሮ የሚያልቅ ባይሆንም፥ ከፓስተር ዳዊት ስሕተት ጋራ የተገናኘበትን ሌላውን ጥቅስ ልናልፈው አይገባም:: ፓስተር ዳዊት "እሱን ስሙት" ብላ እመቤታችን የተናገረችውን ጠቅሶ በሌላ ጽንፍ ቆሞ እኛን ለመተቸት እንደሞከረ፥ ደፍተራ ገለፈት እግሩን በአውደ ምሕረታችን ተክሎ፥ ጭንቅላቱንና ሕሊናውን ግን በነ ማንዴዝ ጽንፍ ላይ አሰልፎ በሚያካሄደው ክህደት፥ ፈጣሪ ዓለምን ለማዳን ተባባሪ ረዳት አስፈልጎት፥ ለዚህም ተግባር እመቤታችን እንደተመረጠች አድርጎ "እሱን ስሙት" የሚለውን ጥቅስ በራሱ ፈጠራ አወላግዶ፥ በገጽ 19 እና በገጽ 101 ላይ አቅርቦታል::

# ፫ኛ. "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ"

እመቤታችን ስለ ወይኑ ማለቅ ጌታችንን ባሳሰበችው ጊዜ፥ "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" ብሎ የመለሰላትን በጥራዝ ነጠቅነት፥ *"እንደ እናትነትሽ ታዝዥኝ እንደሆነ እንጂ ኃይሌን የምገልጽበት ጊዜ ገና አልደረሰም ማለቱ ነው"* ብሎ በገጽ 19 አወላግዶ ካቀረበው በኋላ፥ እንደገና ይህንኑ ጥቅስ በገጽ 101 ላይ *"ኢየሱስ የጊዜውን አለመድረስ የጠቀሰው የእመቤታችንን ማሳሰቢያ ተገቢ አይደለም ብሎ ሳይሆን እውነተኛ ማንነቱን ማለትም አምላክነቱን ከመግለጡ በፊት ተአምር ቢሠራ ተመልካቾች እንደ ማነኛውም ዕሩቅ ብእሲ ገባሬ ተአምር ወይም እነደ አስማተኛ ሊቆጥሩት እንደሚችሉ ስለ አወቀ ነው"* ብሎ በሌላ መንገድ ጠምዝዞ አቀረበው:: በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አስመሳይ አታላይ ነህና አቁም የሚለው ሰው እንደሌለ ስለ ተረዳ፥ አሁን በሱ ቤት ይህን ጥቅስ አምልቶና አስፍቶ አመሥጥሮ መተርጎሙ ነው:: ነገር ግን የቤታችን ትርጉም ደፍተራ ገለፈትን ከነ እምነቱ እንዴት አንጓሎና አበጥሮ ገለፈትና እንክርዳድ እንዳደረገው እንመልከት::

በሊቃውንት አበው አተረጓጎም ግንዛቤ እመቤታችን ያቀረበችውን የወይን ማለቅ ጥያቄ፥ ክርስቶስ የመለሰው "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" (ዮሐ ፪፡፬) ብሎ ነው:: ይህ የክርስቶስ አነጋገር የሚያመራው ቅዱስ ማቴዎስ ወዳሰፈረው ወይንና ጊዜ ነው:: ይህን ጥቅስ የጥንት አበው፥ የእመቤታችንን ምልጃ አንተርሰው፥

“ጽዋውንም አንስቶ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው”(ማቴ ፳፮፥፳፰) ብሎ በአዋጅ የሚሰጠውን ወይንና የሚሰጥበትን ጊዜ ለመግለጽ ሲል ጌታችን አጋጣሚውን እንደተጠቀመበት ነው:: ክርስቶስ በቃና ላይ “ገና አልደረሰም” ያለው ወይኑን “ለአዲስ ሥርአት የሚሆን ደሜ ነው” ብሎ ሥርአቱን ያከናወነባትን ጊዜ ለመግለጽ “ሰአቱ በደረሰ ጊዜ” ብሎ ወንጌላዊው ሉቃስ በምዕ ራፍ ፳፪፡ ከቁጥር ፲፬ እስከ ፳ አብራርቶ የመዘገበውን መሠረት በማድረግ ነው:: የመጻሕፍት ሊቃውንት መተርጉማን፥ “አ እግዚአ በከመ አሜሃ ዘነተ ጽዋዕ እተብ ወቀድስ ወመጡ” (ቅዳሴ ገጽ ፻፷፱ ከቀጥ ፻፲፪ እና ፻፲) ማለትም፡-“አምላችን ሆይ ይህን ወይን፥ ባርከህና ቀድሰህ ይህ ደሜ ነው ጠቱ ብለህ ስጠን” የሚለውንና፥ በቃና ጊዜየ ገና አልደረሰም እያለ ጊዜው ሲደርስ በአዋጅ የሚሰጥበትን ሰአት የሚጠቁም ነው:: ሊቃውንት አበው በመተባበር ጊዜው ወደታወጀበት ደሙ እየጠቆሙ የተሰጠበትን ምሥጢርና ጊዜ ያገናዝቡበታል::

ክርስቶስ እመቤታችን ለጠየቀችው “ጊዜየ ገና አልደረሰም” ብሎ የሰጠው መልስ፥ ለአዲስ ኪዳን የሚፈሰው ደሜ ነው፥ እንኩ ጠጡ ብሎ በአዋጅ የሚሰጠውን ወይን፥ ከቃናው ወይን ጋራ እንዳይቀላቀል ለመለየት ነው:: አልደረሰም ያለውም ይህንን ጊዜ ነው:: እመቤታችን ቃና ላይ ስለሰርጉ ወይን ያነሳቸው ጥያቄ፥ ዘላለማዊ ሕይወት ወደሚሰጠው፥ ወደ አዲስ ኪዳን ሥርአት ሥጋየ ነው ጠጡ ብሎ በአዋጅ ወደሚሰጠው ደሙ የሚጠቁም ነው:: ጌታችን “አልደረሰም” ያለው ይህን ለማሳየት እንጅ፥ ደፍተራ ገለፈት “እውነተኛ ማንነቱን ማለትም አምላክነቱን ከመግለጡ በፊት ተአምር ቢሠራ ተመልካቾች እንደ ማነኛውም ዕሩቅ ብእሲ ገባሬ ተአምር ወይም እነደ አስማተኛ ሊቆጥሩት እንደሚችሉ ስለ አወቀ ነው” ብሎ እንደተረጎመው አይደለም:: ምክንያቱም እመቤታችን በጠየቀችበትና ተአምሩን ከመሥራቱ በፊት በነበሩት ደቂቃዎች መካከል አምላክነቱን የገለጸበት ልዩ ተአምር አልፈጸመም:: ከዚህ ውጭ የሚደረገው ትርጉም፥ ጥራዝ-ነጠቅነትን፥ ባዶ ድፍረትን፥ ተቆጭና አቁም የሚል አካል መጥፋቱንና የቅዳሴውን ይዘት እንኳ የተረዱ ሰዎች ከቤታችን የጠፉበት ዘመን መሆኑን የሚያሳይ ነው::

ከዚህ አንቀጽ ሳንወጣ ደፍተራ ገለፈት የጨመረው ሌላ ኑፋቄ አለና እሱንም እዚሁ እንጨርሰው:: በጠልሰሙ ገጽ 198 ላይ “ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ የሚበልጠውን ዓለሙን ያዳነበትን ጥበቡን ለመፈጸም ተባባሪ እንድትሆነው የመረጠበትን እናቱ ድንግል ማርያምን ከአዳም ኃጢአት ሠውሮ ፈጠራት ማለት እላይ ከጠቀስነው መለኮታዊ መብቱ ጋር የተያያዘ ነው” ብሏል:: ይህ አረፍተ ነገር፥ በኦርቶዶክስ እምነትና ትምህርት የሌለውን በሰው አዕምሮ ላይ ለመጫን ያደረገውን እኩይ ፈጠራ <u>አጋልጧል:: የነገረ መለኮት ጥልቅ ግንዛቤ የሌለውን ሕዝብ አስደንብሮ በራሱ ክህደት ለማሰለፍ ሁሉት ማስበርገጊያ ሐረጎችን በዚህ አረፍተ ነገር አጣምሮ አቀረበ</u>::

- ያቀረበውን የተሳሳተ ትርጉም ሰው እንዳይጠይቀው ከ“መለኮታዊ መብት ጋር የተያያዘ ነው” አለ::
- የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይ በእመቤታችን ላይ ባለው ጽኑ ፍቅር፥ ሳይነቃብኝ ያላንዳች ችግር ይቀበለኛል በሚል ሸፍጠኛ ግምትም “ከአዳም ኃጢአት ሠውሮ ፈጠራት” የምትለዋን ሐረግ ከተተ:: በውስጠ ዘ፥ በውስጠ ወይራና በሠረዝ የቅኔ አይነቶች፥ በለሰለሰ ልምድ ላይ

የተመሰረተው የነ የኔታ ፍስሐ ያንድምታ ያተረጓጎም ስልት፥ ይህ አይነቱን ሽፍጥ አንጓሎ የሚጥል ገለፈት ያደርገዋል:: ይህ አቀራረብ የእመቤታችንን ክብር ከመለኮት መብት ጋራ አቆላልፎ በማቅረብ እጠቀማለሁ ብሎ ባቀረበው ትብትብ "ተባባሪ" (Co-Redeemer) ናትከሚለው ክህደት ውስጥ ገባ::

# ፬ኛ. ተባባሪ (Co-Redeemer)

እመቤታችን ለ፱ኛ ወራት ማኅደረ መለኮት ከመሆን በላይ ከአየር ላንድ በሰማው እጅግ አንሮ በመለጠጥ ሊወጣበት ከማይችልበት አዘቅት ውስጥ ወደቀ! የጥንት ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ዮሐንስ አፈወርቅ "ሁልጊዜ ድንግል የሆንሽ፥ አምላክን የወለድሽ፥ የብርሃን እናት፥ የባሕርያችን መመኪያ" (ሃይ አበው ፷፷፡ ከቁጥር ፴፫-፴፱) እያሉ ነው እመቤታችንን የሚገልጿት:: ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም እመቤታችንን እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከገለጹበት ክብሯ በላይ አንረው ተባባሪ (co-redeemer) ሆነች አይሉም (ሥ ቅ ገጽ ፷፩ እና ፷፪ ከቁ ፻፶፫ እስከ ፺፶፷):: እመቤታችንን ለማዳኑ ተግባር ተበባሪ (co-redeemer) አድርገው የሚያቀርቧት ከኦርቶዶክስ ግንዛቤ ውጭ ያሉ ሌሎች ናቸው:: እግዚአብሔር ዓለምን ለመፍጠርና ለማዳን በፈቀደበት እቅዱ የፍጡርን ተባባሪነት አይሻም:: እመቤታችን ከፍጡራን መካከል ናት:: ስለዚህ ኦርቶዶክሶች እመቤታችን ዓለምን ለማዳን ለተባባሪነት ተመረጠች ብለው አያስተምሩም:: የተመረጠችው በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከሷ ከፍሎ የሚያድንበትን የአዳምን (የኛን) ሥጋና ነፍስ ለመወሐድ እንጅ፥ እሷ በማዳኑ ተግባር እንድትረዳው ተባባሪ co-redeemer እንድትሆነው አይደለም:: ይህ እምነታችንን የሚያስነቅፍ ከኦርቶዶክስነት የሚያወጣ ትልቅ ኑፋቄ ነው::

እመቤታችን "እነሆ ባሪያህ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" በማለቷ እሽታዋን ፈቃዷን፥ ታዝዥነቷን ፍጹም እምነቷን ገለጸች ማለት እንጅ፥ ለማዳኑ ሥራ ተባበረች ማለት አይደለም:: በመፍጠሩም ሆነ በማዳኑ ሥራ ሥምረትና ፈቃድ የእግዚአብሔር ወይም የሥላሴ ብቻ ነው:: ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ቅዱስ ኤፍሬም "እስመ በፈቃዱ፥ ወበሥምረተ አቡሁ፥ ወመንፈስ ቅዱስ" እያሉ እንጅ፥ "ወበ ሥምረተ ቅድስት ድንግል ማርያም" በማለት በማዳኑም በመፍጠሩ ተግባር ላይ የእመቤታችንን ትብብር ነበረበት አላሉም:: ከቅዱስ ኤፍሬም ጋራ ሁሉም ሊቃውንት ይስማማሉ:: እነ ቅዱስ ቄርሎስ "ወደለወ ለዘወረደ ይትመከር ወይትቃረኖ ለሰይጣን ዘሞአነ ቀዳሚ ወተጻብአ በእንቲአነ ወገደፎ መትሕተ ወአዕረቆ እምኃይሉ ወበእንተዝ ግብር መጽአ በሥጋ ዋሕድ ቅዱስ ያርእየነ ከመ ንሳተፍ ንሕነ ተስፋነ ፍጻሜሁ" (ቄር ፸፱፡፳፫) እያሉ ባስተማሩት እመቤታችን ከአዳም ዘር ውጭ፥ ወይም እንደ ክርስቶስ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ዓለም የመጣች ስላይደለችና የመለኮትነት ባሕርይም ስለሌላት፥ ለድሕነቱ ተሳታፊ ናት እንጅ እግዚአብሔር ወልድ ብቻውን በመስቀል ተሰቅሎ ለፈጸመው ለማዳኑ ተግባር ተባባሪ አይደለችም::

እነ ቅዱስ ባስልዮስ ሁሉ “ወሶበ ርእየ ወልድ ከመ በዝንት ኃጢአት ወረደ ወኀደረ በእግዝእትነ ቅድስ ድንግል ማርያም በግብር ዘኢይትነገር ወዘኢይትሐተት ወተጸውረ በክርሳ ፱ተ አውራኃ:: ወነሥአ እምኔሃ ሥጋ ፍጹመ ዘፈጠሮ ለርእሱ እንዘ ሕልው ውስቴታ በፈቃደ አቡሁ ወበሥምረተ መንፈስ ቅዱስ” (ሃይ አበው ምዕ ፴፩፡፱) እያሉ ነው ያስተማሩት:: “ተባባሪ እንድትሆነው” ማለት co-redeemer ናት ብለው የሚያስተምሩት ሰወች እምነትና ስብከት ነው:: ይህ አይነት ትምህርትና እምነት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነገረ መለኮት ሊቃውንት የሚያስወግዝ ነው::

# ፫ኛ. የዘመናችን ፈተና ከጥንቱ ጋር ሲነጻጸር የትኛው ፈተና ይከፋል?

ከዛሬ ፸ ዓመታት በፊት የነበሩ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንት አበው፥ የደፍተራ ገለፈትን ትምህርትና እምነት በማሰራጨት ህዝቡን ላሳሳቱት ለእነ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ፥ አለቃ ሀብተ ወልድንና አለቃ ውቤ ወደቤተ መቅደስ ገብተው እንዲቀድሱ፥ ወንጌልም እንዲያስተምሩ እድል ሊሰጧቸው ቀርቶ፥ ዘመኑ በሚፈቅደው ቅጣት እንዲቀጡ ሕዝቡ ፈረደባቸው:: የኦርቶዶክስ አበው ሊቃውንት እውነተኞች ክርስቲያኖች በመሆናቸው፥ ሕጉ በሚፈቅደው የአካል ቅጣት ከሚቀጡ ይልቅ፥ በተወሰነ ቦታ ተቀምጠው ቀሪ ዘመናቸውን እንዲፈጽሙ ለሕዝቡና ለፈራጆች ባቀረቡላቸው ምልጃ ባንድ ቦታ ተወስነው እንዲቀመጡ ተፈረደባቸው:: ይህ ቅጣት የደረሰባቸው አንዷን የጸጋ አተረጓጎም፥ ደፍተራ ገለፈት ባቀረበው መንገድ በአልፍኖሱ ማንዴዝ አተረጓጎም በማቅረባቸው ብቻ ነበር::

ዛሬ የዋሽንግተን ዲሲ ቅድስት ማርያም ምእመናን እምነቱን አብራርቶ የሚነግራቸውና በእምነቱ ጸንቶ የቆመ ካህን በማጣታቸው፥ የተዋሕዶ እምነታቸውን እጅግ በከፋ የክህደት አይነቶች ጠልስሞ ያወጀባቸው ደፍተራ ገለፈት ቀድሶ እንዲያቆርባቸው ተደረጉ:: ካህናቱም ከዚህ ግለ ሰብ ጋር ለቅዳሴ መሰለፋቸው፥ የተዋሕዶውን ነገረ መለኮትና የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ በማወቅ ከምእመናኑ የተሻሉ እንዳልሆኑ፥ ወይም እንደነ አቶ ቢልልኝ የደፍተራ ገለፈት ደቀ ማዛሙርት የሆኑ፥ ወይም ለነገረ መለኮቱ፥ ለቤተ ክርስቲያናችንና ለታሪካችን ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ፥ የቡድንና የአድማ ስሜት ያሸነፋቸው ሆነው እንዲታዩ አድርጓቸዋል:: ደፍተራ ገለፈትን የሸፈኑበት ምክንያት ከነዚህ ሁሉ ውጭ ስለማይሆን፥ ቤተ ክርስቲያናችን በውስጥ የከፋ ፈተና እንደገጠማት ያሳያል::

የዋሽንግተን ዲሲቅድስት ማርያም ምእመናን የመረጣቸው ባለ አደራ ቦርድ አባላትም የተመረጡት ከሕንጻው ጀምሮ እያንዳንዱ ምእመን እስከ ሚጥላት አንድ ሳንቲም ድረስ በተገቢው መንገድ አግልግሎት ላይ እንዲውል፥ ሕዝቡን ወክለው ካህናቱን በቅርቡ ሆነው እንዲታዘቡና እንዲቆጣጠሩ ነበር:: ቤተ ክርስቲያኒቱን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሚያደርጋት ነገረ መለኮቱና የቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ነው:: እነዚህ

ከፈረሱ ሕንጻው ባዶ ቀፎ እንጅ ቤተ ክርስቲያን አይደለም:: በሩቅ ያለው ፓስተር ዳዊት እነዚህን በመንቀፉ እየተቃወምነው ሳለ፥ ከፓስተር ዳዊት በከፋ ሁኔታ ከቤተ መቅደሱ ውስጥ ሆኖ እስካሁን የዘረዘርኳቸውንና ወደፊትም እያከታተልኩ ለምእመናኑ የምገልጻቸውን የክህደት አይነቶች ያወጀውን ግለሰብ አቅፈው መያዝ እጅግ የሚያስገርም ሆኗል::

ከዛሬ መቶ አመት በፊት የነበሩት ኦርቶዶክሳውያን ምዕመናን የሐሰት ትምህርት በማስተማር አታለውልና ይቀጡልን ብለው የጮኹት ደፍተራ ገለፈት ካቀረባቸው ብዙ አይነት ክህደቶቹ በንዷ ብቻ በተሳሳቱት ደፍተሮች ላይ ነበር:: ከዚህ ውሳኔ ላይ የደረሱትም ዛሬ የዲሲን ቤተ ክርስቲያንን በመምራት እንዳሉት ባላደራ የቦርድ አባላት፥ በተለያዩ ሙያወች አዕምሯቸውን የቀረጹ፥ የቀረበውን ክህደት አንብበው የሚረዱ አልነበሩም:: እምነቱ ሞራሉና ፍቅሩ ስለነበራቸው ሊቃውንቱ ሲናገሩ በመስማታቸው ብቻ ነበር:: የዋሽንግተን ዲስ ቤተ ክርስቲያኒቱ የቦርድ አባላት፥ ማነኛውንም መጽሐፍ አንብቦ ለመረዳት በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙሪያ ከተሰበሰቡት ካህናት ነን ባዮች ይልቅ ጥልቅ ችሎታ እንዳላቸው የታወቀ ነው:: <u>ደፍተራ ገለፈት በቤተ መቅደሳችን ያወጃቸውን ብዙ የክህደት አይነቶች ፍጹም የተሳሳቱ እንደሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍትና በታሪክ የተደገፈ ማስረጃ ገጽ በገጽ አንቀጽ ባንቀጽ ሲቀርብላቸው እርምጃ በመውሰድ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከመጠበቅ ይልቅ ጠልሰሙ በሽያጭ፥ ደፍተራ ገለፈትም በቅዳሴው እንዲቀጥል መስማማታቸው ከዚህ ቀደም ቤተ ክርስቲያናችንን ከገጠማት ፈተና ይልቅ በዚህ ዘመን የገጠማት ፈተና እጅግ የከፋ ሆነ</u>::

በኛ ዘመንም *“ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖትና ተማሕፅኖ”* በሚል ስም የተጠለሰመችው መታሰቢያ እንዲሆናቸው የተሰጣቸው አባት አቡነ ማቴዎስ ያዘጋጁት ጠልሰምም፥ ከደፍተራ ገለፈት ጠልሰም ጋራ ስትነጻጸር፥ የአቡነ ማቴዎስ ጠልሰም የያዘችው ሳይታረም መታለፍ የሌለበይ ትልቅ ክህደት ቢሆንም፥ የደፍተራ ገለፈት ጠልሰም ግን በዓለም ዙሪያ ያለውን ሁሉ ክሕደት ሰብስባ የተሸከመች ከአቡነ ማቴዎስ ጠልሰም ጋራ ከንጽጽር እጅግ የራቀች ናት:: <u>የዲሲ ርዕሰ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሊቀ ማዕምራን ካሳየ በአቡነ ማቴዎስ አንዷ ስሕተት ምክንያት፥ የደብረ ሊባኖስ ሊቃውንት የተሰማቸውን ስሜትና የከፈሉትን መስዋዕት ተመልክተዋል:: ጠልሰሟም ስትቃጠል እዚያው የነበሩ የአይን ምስክር ናቸው:: ዛሬ እራሳቸው ሊቀ ማዕምራን አማረ ካሣዬ በሚመሯት ደብር፥ አቡነ ማቴዎስ ከፈጸሟት አንዷ ስሕተት ይልቅ እጅግ የከፋና የሰፋ ስሕተት የተሸከመች ጠልሰም በራሳቸው በአቡነ ማቴዎስ ስም ደፍተራ ገለፈት ጠልስሞ ያቀረበውን ለሕዝብ ሲያሰራጭ መተባበርና፥ ደፍተራ ገለፈትንም አቅፈው ይዘው አብረው መቀደሳቸው፥ ቤተ ክርስቲያናችን ያለችበት ሁኔታ፥ ከቀድሞው ይልቅ እጅግ በጣም እጅግ የከፋ እንደሆነ ያረጋግጣል</u>::

የተለያዩትን ሲኖዶሶች አስታርቆ አንድ ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት የሚደገፍ ቢሆንም የሚመሯትን ደብር ተብትቦ ከያዛት የክህደት ቀውስ ሳያላቅቁ፥ ክህደቱን እየዘራ ያለውን ግለሰብ አቅፈው ይዘው አብረው እየቀደሱ፥ የነገረ መለኮት የቀኖናና የታሪክ ጥያቄ ያዘለውን ይህን ከባድ ኃላፊነት በምን ሞራላቸው፥ የውሳኔ ችሎታቸውና ታማኝነታቸው ከግብ ያደርሱታል ተብሎ ይገመታል? ቤተ ክርስቲያናችን ለእምነታቸው፥ ለታሪካቸው ተላልፈው የሚሰው የብዙ ሊቃውንት አበው እናት

እንዳልነበረች ሁሉ፥ ዛሬ ሊቀ ማእምራን አማረ በደብራቸው የተነሰነሰውን ኑፋቄ ሳያጠሩ በዚህ ኃላፊነት መሰለፍ ቤተ ክርስቲያኒቱ የወላድ መካን የሆነችበት ዘመን እንደሆነ የሚያሳይ ነው::

ፓስተር ዳዊት በውጭ ሆኖ ያወጀውን ፕሮቴስንታታዊ ጂሐድ፥ ደፍተራ ገለፈት በውስጥ ሆኖ ካወጀው ጋራ ስናነጻጽረው የትኛው ይከፋል? ፓስተር ዳዊት እንደ ደፍተራ ገለፈት በዋሽንግተን ዲስ ቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ ውስጥ ይህን ጉድ ይዞ ብቅ አላለም:: እንደ ደፍተራ ገለፈትም ከራሱ እስከ ጥፍሩ በኦርቶዶክሶች ሊቃውንት መለያ ልብስ ራሱን ሸፈኖ አልቀረበም:: በሊቃውንቱ ማዕረግ ስም ርዕሰ ደብር ብሎ ራሱን አልሰየመም:: ሰተት ብሎ ወደ ቤተ መቅደሳችን አልገባም:: እንደ ደፍተራ ገለፈት የተጸየፋቸውንና ስሕተት አለባቸው ብሎ ያጣጣላቸውን መጽሕፍት እየተጠቀመ እሰብካለሁ፥ አጠመቃለሁ፥ ቀድሼ አቆርባለሁ አላለም:: ክሕደቱን ደብቆ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነገረ መለኮት ታማኝነት ያለው መስሎ ወደ ሕዝቡ አልቀረበም:: እንደ ደፍተራ ገለፈት አስተምራችኋለሁ እያለ የሚያደናግራቸው ምዕመናን እምነቱን ጠልቀው አለማወቃቸውን ተገንዝቦ፥ ዘመኑ ክፉ፥ ቤተ መቅደሷም ባዶ እንደሆነች ተረድቶ፥ እጽፍ ድርብ ጥቅሙንና አላማውን ለማካሄድ እቅዱን ዘርግቶ፥ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ለትክክለኛ እምነታቸው ትክክለኛ አገልግሎት እንዲውልላቸው የሚያጠራቅሙትን ሙዳየ ምጽዋት ላቀደው ደባ ማከናወኛ አድርጎ አልተጠቀመበትም:: መጠልሰሚያ ወረቀቱን አልገዛበትም:: መጠልሰሚያ ብዕሩን አልቀረጸበትም፥ ቀለሙን አላዘጋጀበትም:: እንደ ደፍተራ ገለፈት አቶ ቢልልኝን ከመሳሰሉ ሰዎች ጋራ መክሮና አስጠልሳሚወቹን ሁሉ በዙሪያው ካሰባሰበ በኋላ፥ የቤተ ክርስቲያናችንን ነገረ መለኮት፥ የአገራችንን ታሪክ የሚደመስሰውን የክህደት ጠልሰሙን ተሰምቶ በማይታወቅ ከአቡነ ማቴዎስ ጠልሰም በከፋ *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* በሚል ርዕስና *"ክርስቶስ ፍጡር ወይስ ፈጣሪ"* በሚሉ ርዕሶች በምእመናኑ ላይ አልጠለስመባቸውም:: ከጠለሰመባቸው በኋላም፥ እፍዝዞና አደንዝዞ በሃይማኖታቸው፥ በቤተ ክርስቲያናቸው፥ በታሪካቸው ላይ የፈጸመው ዘመቻ ሳያንሰው፥ ያንኑ የጠለሰመባቸውን ጠልሰም ጥሩና ጠቃሚ የሃይማኖት መጽሐፍ ናት ግዙኝ ብሎ በማቅረብ፥ ገንዘባቸውንም አልዘረፋቸውም::

***ራሳቸው በጻፉት ላይ የመሰከሩትን ደብቀው፥ ከኦርቶዶክስ ትምህርትና እምነት ለይቶ ከሮማ ካቶሊክ ጋራ አንድ የሚያደርገንን ሳያርሙ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያንና ከመላው ኦርቶድክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋራ አንድ ነን ብለው የሚፈራረሙትን፥ ለነገረ መለኮት መዛባት ለታሪክ መቃወስ ደንታ ሳይሰማቸው ለራሳቸው ሐውልት ሸንጣቸውን ገትረው የሚታገሉትን አቡነ ጳውሎስን፥ ትልቅ ሐዋርያዊ ተልእኮ ፈጸሙ ብሎ እንደ ደፍተራ ገለፈት ፓስተር ዳዊት በጠልስም አላሞገሳቸውም::***

ቢሰሙኝስ፥ ቢአውቁብኝስ አይሾሙኝ አይሽልሙኝ በምን ይጎዱኛል? በምንስ ይጠቅሙኛል? በሚል ደካማ አስተሳሰብ፥ በሃይማኖታቸው ጸንተው እውነቱን የመሰከሩትን አቡነ ሽኖዳን ከሐዲ ናቸው እያለ እንደ ደፍተራ ገለፈት በጠልሰሙ አልዘለፋቸውም:: በውጭ ተሰደው በሚኖሩት ኢትዮጵያውያን አባቶች ላይም ከአቡነ ሽኖዳ ጋራ አንድ ላይ ደምሮ አልዘመተባቸውም:: <u>ፓስተር ዳዊትን የምንወቅሰው፥ አገራችንን ዳር ድንበር አሳጡ፥ እኛንም ከፋፈሉን፥ የዲሞክራሲ መብታችንንም ገፈፉን እያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሚጮህባቸው በዘመናችን መሪዎች ላይ አንዲት ቃል ሳይናገር፥ አገርና ወግን ባልጎዱ ታሪክ ባልናዱ ሃይማኖት ባልካዱ ከዚህ ሁሉ ርቀው ባሉት ገዳማውያን ላይ፥ በቤተ ክርስቲያናችን ላይና በሊቃውንት አበው በነ ቅዱስ ባስልዮስ፥ ጎርጎርዮስ፥ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይማናታችን ላይ ለምን</u>

ዘመተባቸው በሚል ነው:: አንደበታቸውን በጾምና በጸሎት የዘጉትን፥ ከሁሉም ቀርው ያሉትን ከአምላካቸው ሌላ መመኪያ የሌላቸውን ገዳማውያን አባቶችን በመዝለፉ፥ በኦሮቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ብቻ ሳይሆን፥ ፓስተር ዳዊት በሰሚና በተመልካች መወቀሱ መገሰጹና መከሰሱ ተገቢ ነው::

ይሁን እንጅ የኦርቶዶክስ ሊቃውንት አበው የምናየውን እውነት ያለ አድለዎ እንድንናገር፥ ዘረኝነትን፥ ጎሰኝነትን፥ ድርጅታዊነትንና አድመኝትን አጥብቀን እንድንቃወም ያስተማሩንን ልንረሳ አይገባንም:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ነገረ መለኮቱን ጠልቀው ሳይረዱ ጥቅስ በመናጠቅ መለያየት የሚፈጥሩትን መክረንና መንገዱን አሳይተን አስማምተንና አፋቅረን በተሰጣቸው ጸጋ እንዲሰማሩ እንድናደርግ “ወዘንተ ረከብነ ውስተ ትምህርተ ዐላውያን እለ ኢየኀብሩ በበይናቲሆሙ ወለኩሎሙ ፩ዱ ንባቦሙ በክህደት ዘያጸንን ኀበ ርስዓት ወበእንተ ዝንቱ ይጻልኡ በበይናቲሆሙ ወይታቃወሙ ወይትሜክሁ ላዕለ ነገረ ትምህርቶሙ ለአበዊነ እለ ተጋብኡ በኒቅያ” (ሃይ አበው ፷፱፡፷፬) እያሉ ነፍሳቸውን ይማረውና የሊቃውንቱ መምሕራን እነ የኔታ ቢረሳው መንገዱን አሳይተው ነበር:: የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አበው ጉባዔ ትምህርት የሚያዝዘውን ጠብቆ ማነው ሓላፊነቱ የተወጣ? ዛሬ በውስጧ ያሉ ሰዎች፥ የየራሳቸውን ድርጅት አልፈጠሩባትም? ለፈጠሩትስ ድርጅት ሲሉ የሚጮኹትን ለቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ደህንነት የጮኹ እያስመሰሉ የዋሑን ሕዝብ በማደንቆር ላይ አይደሉምን? ቤተ ክርስቲያናችን የምታስተምረውን ነገረ መለኮት ለይተው ሳያውቁ ከውጭ በቀላወጡት፥ ከየመንደሩም በሰሙት ነገረ መለኮቱን ከሚያቃውሱት ጋርስ አልተባበሩም? ቤተ ክርስቲያናችንም አሐቲ ቅድስት ጉባዔ እንተ ሐዋርያት እያለች የኖረችውን በማፍረስ ላይ ያሉትን ስድብና ዘለፋ በመፍራት፥ ከመገሰጽ ይልቅ ከነሱ ጋር አልተሰለፉም? ቤተ ክርስቲያናችንን ለራሳቸው ድርጅት ሕልውና፥ ለግላቸው ጥቅም፥ ደፍተራ ገለፈትን ለመሳሰሉ ከሐዲና አድማ ፈጣሪ መጋረጃ አላደረጓትም? በቅርቡ በተግባር ተፈጽሞ ያየሁትን ለበቂ ማስረጃነት በዚህ አጋጣሚ እጠቅሳለሁ::

በሥልጣን ዘመናቸው አቡነ ጳውሎስን ለማስቀመጥ፥ አቡነ መርቆርዮስን ያስወገዱትን አቶ ታምራት ላይኔን ወቅሰን (http://www.medhanialemeotcks.org/pdf/FIKARE.pdf) ነበር:: ጌታችን በወንጌሉ እንደገለጸው፥ ክርስቲያን ሆኛለሁ የሚል ሰው የሚወቀስበት ነገር ካለ፥ ያንን ሳያስተካክል ድኛለሁ ቢል ውሸት ነው” (ማቴ ፭፡፳፫) እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሰው መጀመሪያ ለበደለው በደል ይቅርታ መጠየቅ ያለበት፥ የበደለውን ድርጅትም ይሁን ግለሰብ እንጅ ክርስቶስን አይደለም:: ይህን ሳይፈጽም የክርስቶስን ድምጽ ሰምቻለሁና ዳንኩ ማለትና ወደቁርባኑ መቅረብ እራስንም ሕዝብንም ማታለል ነው:: የተቀበላቸውም ድርጅት ለበደልከው በደል ይቅርታ ጠይቅ ሳይል ሽፍኖ መያዝ ለስሕተቱ ተባባሪ መሆን ነው:: ይህን ጠቅሰን በአቶ ታምራት ላይኔ ላይ ትችት አቅርበን ነበር:: አቶ ታምራት ላይኔ የሰሩት ስሕተት የማይካድ እውነት ከሆነ፥ የበደሉትን ሕዝብ ይቅርታ ሳይጠይቁ፥ እንዴት ክርስቶስ ይቅር አለኝ እያሉ ይሰብካሉ? “የበደለ ይቅርታ ይጠይቅ የተበደለ ይቅር ይበል” እያለ ያስተማረ ክርስቶስ እንዴት ይህን በሕሊናቸው አልሳለባቸውም? በሚል ለተነሳው ጥያቄ ተገቢና ክርስቲያናዊ ነው ከማለት ይልቅ፥ የተጠጉት ድርጅት ሸፈናቸው፥ እሳቸውም ጸጥ አሉ:: ጥቂቶቹ እንዲያውም ለምን ይቅርታ ይጠይቁ ይባላሉ በማለት አጉረመረሙ:: በሌላ በኩል ደግሞ “እሳቸው ክርስቶስን ተከትለዋልና ይቅርታ መጠየቅ የለባቸውም” የሚለውን አስተሳሰብ፥ ብዙው ህዝብ ከአገር ከወገን ከእውነትና ከክርስትና

ይልቅ ለግለ ሰብና ለድርጅት ቅድሚያ መስጠት እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ ተቃወመ:: በዚህ እየተገረምን ሳለን::

አሁን በቅርቡ ደፍተራ ገለፈት ባወጀው ጀሐድ፥ በአቶ ታምራት ላይኔና በሽፈናቸው ጎራ ከተፈጸመው ስሕተት የባሰ ስሕተት በዋሽንግተን ዲስ ቅድስት ማርያም በኛው ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ:: ኮምኒስታዊው መንግሥት ያለአግባቡ እየወሰነ ሕዝቡን ባሰቃየበትና በፈጀበት ሕግ ተሰልፈው ሲቆርጡና ሲፈልጡ ከነበሩት አንዱ በዋሽንግተን ዲስ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመዘምርነት በአስተዳደር ቦርድ አባልነትና፥ በሕግ አማካሪነት እያተራመሱ ያሉት አቶ ቢልልኝ ናቸው:: አቶ ቢልልኝ፥ ምትክ የማይገኝላቸውን ታላቁን አባት አቡነ ቴዎፍሎስን በወታደር ማርሽ ከመንበራቸው አውርዶ በሰማእትነት የገደለና፥ በምትካቸው አቡነ ተክለሃይማኖትን በመተካት ቤተ ክርስቲያናችንን ያዋረደውን ኮምኒስታዊውን ሕግ ያራምዱ የነበሩ ሰው ናቸው::

ይህ መንግሥት ደርግ ከሚከሰስበት በደልና ግፍ ይልቅ እጅግ በከፋ በደለኛና ግፉኛ አርጎ በውስጥም በውጭም ያለው ወገን ይመለከተዋል:: ዜጎችን የሚቀጣውም ብሔራዊና ታሪካዊ በሆነ ሚዛናዊ ፍትህ ላይ ባልተመረኮዘ፥ በቂም በበቀልና ከራሱ ፖለቲካዊ ጥቅም አንጻር በሞሆኑ፥ በዚህ መንግሥት እጅ ከወደቁት ወገኖቻችን ጀምሮ በውጭ የተበቱኑትን ሁሉ በዚህ መንግሥት እጅ እንዲወድቁ ማንም ሰው የሚመኝ አይኖርም:: ሆኖም ደርግ ይደበድብበት የነበረውን ብትር፥ ያስርበት የነበረውን ሰንሰለት፥ ይገልበት የነበረውን ጥይት፥ ይጋልብበት የነበረውን የአብዮት ፈረስ ልጓም ይቃኝ ይመራና ይጎትት የነበረው አብዮታዊው ሕግ ነው:: ይህን ሕግ ይቃኙ፥ ያስተካክሉና ይጎትቱ ከነበሩት አንዱ አቶ ቢልልኝ ናቸው:: ይህን አብዮታዊ ሕግ እየጠቀሰ ደርግ ከፈጸመው በደል ነጻ ነኝ ማለት አይችሉም:: ወደዚህ አገር የተሰደዱትም ይህ መንግሥት የፈጽመውን በደል ተቃውመው ሳይሆን፥ እሳቸው ይቃኙት በነበረው ሕግ በፈጸሙት ወንጀል ከሚደርስባቸው ቅጣት ለማምለጥ ነው:: ይህም ባልከፋም ነበር:: ወደ እዚህ አገር ከመጡ በኋላ በበደሉት በደል ተጸጽተው ንስህ ገብተው የክርስቶስን ሥጋ ደም መቀበላቸውም ተገቢ ነበር:: ሆኖም አሁን በቅርቡ ደፍተራ ገለፈት የፈጸመውን እጽፍ ድርብ በደል በጠልስም ያቀረበውን ታትሞ ለሕዝብ እንዲሰራጭ በመተባበራቸው እጅግ የከፋ በደል አቶ ቢልልኝ ፈጽመዋል::

ራሱ ጠልሰመኛው "አቶ ቢልልኝ የመጠልሰሙን ንድፍ በጥንቃቄ በማንበብ አስተያየቶችን ከመለገሱ በላይ አጻጻፉ ለማንም ግልጽ እንዲሆን የሰጠኝ ምክር በሥራ ላይ ውሏል" ይልና "ይህም ብቻ አይደለም" ብሎ፥ "ወደፊት የአቶ ቢልልኝ አስተዋጽኦ ሌሎችን ተመሳሳይ የክህደት ጠልሰሞችን ለመጠልሰም የተደገሰ ውል" እያለ እንደመሰከረው፥ በጠልሰሙ ላይ የሰጡት አስተዋጽኦ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነገረ መለኮትን ንዷል:: ቤተ ክርስቲያናችንን አዋርዷል:: ታሪካችንን አፋልሷል:: ምሕረተ አብ አሰፋ ፕሮቴስንታንታዊ ጂሀድ ታወጀባቸው ብሎ በጠቀሳቸው በቅዱሳን አበው ላይ የከፋ ጂሀድ አውጇል:: በክርስትናችን ይህን ያህል በደል የፈጸመ ሰው ቀርቶ፥ አንድ ግለ ሰብ የበደለ፥ በደሉ ከተረጋገጠ፥ ወደ ቁርባን ሊመጣ ይቅርና ለበደለው ይቅርታ ሳይጠይቅ በድልሐል እየተባለ ሰብሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊመጣ አይገባውም:: "ወንድምህ በአንተ ላይ ቅሬታ ካለው አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር

ታረቅ በኋላም መባሕን አቅርብ”(ማቴ ፭፡፳፫-፳፬) ይህን የሚያደርግ ከሆነ ሃይማኖት የሌለው፥ እምነቱንና ቤተ ክርስቲያንን ሕቡዕ ለሆነ አላማ ለመጠቀም የተዘጋጀ ነው ማለት ነው::

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ፥ መጽሐፏ ጠቃሚናት ብለው ያወጁትን ዶክተር አክሊሉን፥ አርመውና አስተካከለው ትክክል ነው ብለው ያቀረቡትን አቶ ቢልኝንና ጠልሰመኛውን ደፍተራ ለመሸፈን፥ ዲሜጥሮስ የሚባል ሰው የፈጸመው አይነት ስሕተት በዋሽንግተን ዲሲ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ላይ ተፈጸመ:: ሙሉ ታሪኩ በሐዋርያት ሥራ ምዕ ፲፱፥፳-፵፩) የተመዘገበው ነው:: ዲሜጥሮስ ወርቅ እየሰራ የሚሸጥ የጥቅም ሰው ነጋዴ ነበር፡፡ በሱ እጅ ሥራ የአርጤምስ ቤተ መቅደስ እጅግ ያጌጠች ነበረች:: እነ ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ሁሉ ወደ ክርስትና እንዲመጣ ባደረጉት ስብከት በአርጤምስ ቤተ መቅደስ የተደረደረው የዲሜጥሮስ ሥራ ተናደ:: ዲሜጥሮስ ጥቅሙ እንዳይቀርበት፥ የጥቅም ተካፋዮቹንና የአርጤምስን ወዳጆች ሰበሰበና ክስረቱን ከአርጤምስ ክብር ጋራ ቀላቅሎ ታላቂቱ አርጤምስ ተሰደበችላችሁ የሚል ዘዴውን አሰራጨ:: “ወእለሰ ይበዝኁ እምኔሆሙ ኢየአምሩ በእንተ ምንት አንገለጉ”(፲፱፡፴፪) እንዲል፥ በነገሩ ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸውን የዋሐን ሰዎች ስሜት ሳይቀር ቀሰቀሰና የፍላጎቱ ደጋፊዎች አርጎ አሰለፋቸው:: ደፍተራ ገለፈትም ብዙ ክህደት የጠለሰመበትን ሸጦ ለመጠቀም ሲል፥ በእመቤታችን ላይ ያለውን የሕዝቡን ፍቅርና ክብር ለሸፍጡ ተጠቀመበት:: “እመቤታችንን ኃጢአተኛ ናት ብየ ባለመጻፌ ይኹውላችሁ እንዲሆንኩላችሁ” ብሎ አወናባጅ ወሬ ፈጠረ:: የሚያስተጋቡለትንም አዘጋጀ:: “እንተ ታስተርኢ ሃይማኖተ ይነግር ብእሲ ጻድቅ፥ ወሰማዕተ እኩያን ሕብል”(ምሳ ፲፪፡፲፯) ማለትም፡- ትክክለኛ ሰው ሃይማኖትን የምትገልጽ ይናገራል:: የሐሰት ምስክሮች ሸፍጥን ይመሰክራሉ” የሚለውን ቃል ሰምተው የማያውቁ ተባባሪዎቹም እሱን ለመሸፈን የፈጠረውን መላ በማሰራጨት ሕዝቡን እያስበዘበዙ፥ ቤተክርስቲያናችንንም እየናዱ ናቸው::

ደፍተራ ገለፈት በዚህ እኩይ ዘዴው ከገባበት ወጥመድ ለማምለጥ ቢሞክርም፥ ከቤተ መቅደስ መውጣት ያለበት “ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት” በሚል ርእስ ለንግድ ባዘጋጀው ጠልሰም ውስጥ ደርድሮ ባቀረባቸው ክህደቶቹ ነው:: ምክንያቱም “እመቤታችን ያለጥንተ አብሶ ተወለደች” የሚለውማ ከዛሬ ሰባት አመት በፊት ተጥንቶ ከኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት ውጭና የሮማ ካቶሊኮች ብቻ እንደሆነ የኛ፥ የግብጽ፥ የሶርያ፥ የአርሚኒያ የሕንድና የመላው ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ትምህርት እና እምነት እንዳልሆነ በቤተ ክርስቲያናችን ሠርጎ የገባ ክህደት እንደሆነ በቃልም በጽሑፍም ተረጋግጧል:: ደፍተራ ገለፈትን ከቤተ መቅደስ ይውጣ የምንለው፥ “እመቤታችን ያለጥንተ አብሶ ተወለደች” ተብሎ በስሕተት የገባውን ትምህርት እንደ መግቢያ ቀዳዳ ተጠቅሞ፥ ከአቡነ ማቴዎስና ከውጭ በኮረጃቸው ጠልሰሚን ሞልቶ ባቀረባቸው ክህደቶቹ ነው::

የማያውቅ ሰው ለማያውቀው ነገር አራሚና አሻሿጭ ሆኖ አይቀርብምና፥ በጠልሰሚ የተባበሩና ያሻሻጡ ሁሉ ጠልሰሚ ለተሸከመችው ክህደት ተጠያቂዎች ናቸው:: አስተካክለውና አርመናል ብለው ያቀረቡትን፥ አናውቅም ማለት አይችሉም:: ከዚያም ወዲህ ጠልሰሚ የተሸከመችውን ክህደቶች በተለያዩ ድሕረ ገጾች ላይ በተለያዩ ርእሶች ባቀረብናቸው ጦማሮች፥ የደፍተራቸውን የክህደት አይነቶችን ብዛት ሳያነቡ፥ ወይም ሳይሰሙ አልቀሩም:: ባቀርብናቸው ጦማሮች የተገለጹትን ዓበይት ነገሮች፥ አርመውና

አጣፍጠው ለሽያጭ ካቀረቧት ከደፍተራ ገለፈት ጠልሰም ይዘት ጋራ አነጻጽረው፥ ልክ ነው ወይም ውሸት ነው ማለት ሲገባቸው፥ ጆሯቸውን ዘጉ አፋቸውንም አፈኑ:: የክህደቶችን ይዘት ያረሙበትና ላንባቢም አጣፍጠው ለሽያጭ ያቀረቡበት ችሎታቸው፥ እውቀታቸው ሞራላቸውና ወኔያቸው የት ጠፋ? ከራሳቸው ጀምረው የተሳሳተውን አርመው ለሕዝቡ ትክክለኛውን ነገር ከመግለጽ ይልቅ፥ በሳንቲም ድቃቂ አናምነውም፥ በአስተዳደራችን አይገባብንም ብለው የሸሹትን ሲኖዶስ፥ ዛሬ እነሱ የገቡበትን ክህደትና በደል ለመሸፈን እንደመሳሪያ ሊጠቀሙበት መሞከራቸው ተመልካችን ሳያስገርመው አይቀርም::

ሕዝቡ የቀረቡትን ጦማሮች እያነበበ ታዝቦ እየሳቀባቸውና፥ እኛም በተለያዩ ርዕሶች የተዘጋጁትን ጦማሮች በተከታታይ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ሳለን፥ “ፓስተር ዳዊት በነገረ መለኮቱ፥ በትውፊታችን፥ በቅዱሳን አባቶቻችን፥ በሊቃውንቱ በነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፥ ቅዱስ ባስልዮስና እና ጎርጎርዮስ ላይ የጂሐድ አዋጅ አወጀባቸው” ብሎ በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ ላለው ሕዝብ ምሕረተአብ አሰፋ ተማጎጽኖ ያአቀረበው ደረሰን:: ምሕረተአብ አሰፋ እንዳለው ፓስተር ዳዊት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ያወጀው ጂሀድ፥ እኛ ከዚህ ሆነን ከምንቃወመው ከደፍተራ ገለፈት የክህደት ጂሐድ ጋራ ያንዲት ሳንቲም ሁለተኛ ገጽ ከዚያም እጅግ የሰፋ ገጽ ያለው ሆኖ አገኘነው:: ንጽጽር ውስጥ ገብተን ይህችን ጦማር እንድናዘጋጅ ያደረገንም የምሕረተአብ አሰፋ ተማሕጽኖ ነው:: አንባቢ ተቆርቋሪና ታዛቢ የቀረበውን ንጽጽር በጥንቃቄ ካነበበ በኋላ የትኛው እንደሚከፋ ያላንዳች አድለዎ በቅዱሳት መጻሕፍት የተቃኘ ፍርዱን ይሰጥ ዘንድ በመጠቆም በዚህች ጦማር ያቀረብኩትን ሐተታ እደመድማለሁ::

# ፯ኛ. ያለ አድለዎ እንፍረድ

“መዳልዎ ዓመጻ ርኩስ በኀበ እግዚአብሔር፥ ወመዳልዎ ጽድቅሰ ኅሩይ ሎቱ”(ምሳ ፲፩፡፩)::
ማለትም፡- “በአድለ□ የሚደረግ ፍርድ በፈጣሪ ዘንድ የተጠላ ነው::ሚዛናዊ ፍርድ ግን የተወደደና የተመረጠ ነው” ይህ አባባል በተለያዩ እምነት ድርጅቶችና ከእምነት ውጭ ላለ ሁሉ ሊጠቀምበት የሚገባ ሰው ከእንስሳ የሚለይበት ሰባዊ የተፈጥሮ ሕግና መመሪያ ነው::

ቀድሞ ኢትዮጵያን ሲመሩ የነበሩ አባቶቻችን ኢትዮጵያን ከወራሪ ጠላት የጠበቋት፥ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አበውም የተዋሕዶ ሃይማኖትን በመናፍቃን ትምህርት ከመበረዝ ጠብቀው ያቆዩልን፥ ያለ አድለ□ በሚወስኑት ሚዛነዊና ሰባዊ ፍርዳቸው ነበር:: ከውጭ ለሮማውያን ወኪል ሆኖ የመጣውን እልፎንሱ ማንዴዝንና፥ ለእንግሊዞች ወኪል ሆኖ የመጣውን ሳሙኤል ጎባትን አባቶቻችን ያባረሯቸው ኢትዮጵያውያን ስላልሆኑና በሃይማኖትም ስለማይመስሏቸው አልነበረም:: ኢትዮጵያውያንን ለመበታተን በተሸከሙት መርዝ ነበር::

እነ አጼ ዮሐንስና በዘመናቸው የነበሩት እነ መላከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ከውስጥ ህዝብ ለመከፋፈል ክህደት ያሰራጩ የነበሩትን ኢትዮጵያውያንን እነ አለቃ ሀብተ ወልድን፥ አለቃ ውቤን የመሳሰሉ ደፍተራ ገለፈቶችን ኢትዮጵያውያን ቢሆኑም ተመሳሳይ ጥፋት በመፈጸማቸው በአልፎኑስ ማንዴዝና በሳሙኤኤል ጎባት ላይ የወሰኑትን ውሳኔ ያለ አድለዎ ወስነውባቸዋል:: በቅርቡ በኛ ዘመንም አቡነ ማቴዎስንም በፈጠሩት ስሕተት ከገዳሙ ተባረዋል::

ፍሬምናጦስንና ኢዲስዮስን፥ ከዚያም ተሳቱ ቅዱሳንን የተቀበሉት፥ ያለፈቃዳቸው የተወለዱበትን አገር እንዲለቁ ያደረጋቸውን ሁኔታ በማየትና በደረሰባቸው በደል ነበር:: በመጀመሪያ ወደ አገራችን የገቡትንም ሙስሊሞች የተቀበሏቸው፥ ወገኖቻቸው በግፍ ስላሰደዷቸው በሰባዊ ሚዛናዊ ፍርዳቸው እንጅ ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ ወይም በሃይማኖታቸው ሙስሊሞች ሆነው አልነበረም::

በተቃራኒው ከእስፔን ከእንግሊዝ አገር በመጡት ሰዎች ላይ የሰጡትን ሰባዊ ውሳኔ ያለ አድለዎ ለመወሰን ነው:: በመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው የመጡትንም ሙስሊሞች የተቀበሏቸው ለተሳቱ ቅዱሳን የሰጡትን መስተንግዶ ሚዛናዊ ለማድረግ ነው:: ይህ የሚያስተምረን በዚያ ጨለማ ዘመን የነበሩ ኢትዮጵያውያን እውነትንና ሃይማኖትን ዜግነትን ቋንቋንና ጎጥን ለሰሳሳተ ጊዜአዊ ጥቅምና ስሜታቸው ሳይጠቀሙ በእውነትና በሰባዊ ሚዛናዊ ፍርድ ላይ ብቻ በተመሠረተ ግንዛቤ ይፈርዱ ስለነበረ ነው::

የደብረ ሊባኖስ ሊቃውንት አበው ከደብረ ሊባኖስ ይውጡልን ብለው በአቡነ ማቴዎስ ላይ የፈረዱባቸው፥ አቡነ ማቴዎስ በገዳሙ ውስጥ ቢወለዱና፥ ገዳሙ ቢያሳድጋቸውም፥ የተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያቃውስ ነገር ሲያደርጉ በመገኘታቸው፥ የገዳሙ ሰዎችም ልጃችን ነው አብሮ አደጋችን ነው ብለው አልሸፈኗቸውም:: በእነ አጼ ዮሐንስ ዘመንም ከቤተ ክርስቲያን እንዲወጡ የተደረጉት እነ አለቃ ውቤ ባሉባልታና በጫጫታ በአድማ የሚሸፍናቸው ዘመድ አዝማድ አብሮ የበላ ወዳጅ ሳይኖራቸው ቀርቶ አልነበረም:: አድለወ በሌለው ኢትይጵያዊ ሚዛናዊ ፍርዳቸው ነበር::

ዛሬ ከላይ በንጽጽር ከተጠቀሱት ሸፍጠኞችና አጥፊዎች የከፋ እጽፍ ድርብ በደል በታሪካችንና በሃይማኖት ላይ የፈጸመውን ደፍተራ ገለፈትን" አገር ማለት ጎጥ፥ ሃይማኖት ማለት ጎጥ፥ ቤተ ክርስቲያን ማለት ጎጥ፥ ጎጥ፥ ጎጥ፥ ጎጥ፥ እየተባለ የሚሰበክበት ዘመን ስለሆነ የዋሸንግተን ዲስ ቅድስተ ማርያም መሪዎችም ከላይ የተዘረዘረውን የተደራረብ ክህደት የፈጸመውን የከፋ ክህደትና ሸፍጥ በማሰራጨት ያለውን ደፍተራ ገለፈትን ሸፍኑት:: በሃይማኖት፥ በቤተ ክርስቲያን በታሪክ ላይ ምንም በደል ያልፈጸሙትን የእድሩን አባላት ከነበሩበት በማስወጣት፥ በክረምት በብርድ፥ በበጋ በሙቀቱ እንዲቀጡ፥ ምንም ሕጸጽ የሌለባቸውን አባ መአዛንም ከቤተ ክርስቲያን እንዳይደርሱ ማድረግ መለየት፥ ምን አይነት ፍርድ ነው? እጅግ በጣም የከፋ ዘመን!

ክርስቲያኖች ነን የምንል ደግሞ ከዚያ የበለጠ እጽፍ ድርብ ኃላፊነት አለብን:: ነገሮችን በሚዛናዊ ፍርድ እንድንመለከትና ሕይወታችን በእውነት ላይ እንዲመሠረት "እውነት ነጻ ታወጣችኋለች" እያለ ባስተማረን በክርስቶስ እናምናለን ብለናል:: ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንሄደውም "ይኩን ነገርክሙ እመሂ እወ፡ ወመሂ አልቦ፡ ወፈድፋደሰ እምእሉ እምእኩይ ውእቱ" (ማቴ ፭፡፴፯) የሚለውን ሲነበብ

እንሰማለን:: ይህም ማለት፡- አዎንታ ለተመላበት ነገር ሁሉ ቃላችሁ አዎን ይሁን:: ከአወንታ ጋር የተጋጨ ከሆነ ደግም አዎንታ አይደለምና፥ አይደለም በሉ:: ከነዚህ መስመሮች የወጣ ሕሊና ግን በክፋት የቆሸሸ ነው” እያለ አጠንክሮ የነገረንን እንከተላለን:: በዚህም አምነን ተጠምቀናል፥ ቆርበናል:: ይህም ማለት ያለ አድለወ ለመፍረድ ሚዛናዊ ሕሊናችን ከማያምን ይልቅ የበለጠና የላቀ የሞራልና የመንፈስ ችሎታ አለን ማለት ነው:: ንስሐም ከዚህ ውጭ ሌላ ትርጉም የለውም:: ተረጋግጦ በፊታችን የተቀመጠውን መረጃ (Empirical Proof) እያየን፥ በድርጅት በጓደኝነት በጎጥ፥ በክፍለ አገር ልጅነት ስተተኛውን አቅፎ መያዝ፥ ካቀፍነው በደለኛ እጅግ የከፋ በደለኛ መሆን ነው::

ምን አገባኝ ብሎ መሸሽም በሕይወት እያሉ ራስን በራስ መቅበር ነውና፥ ያልሆኑትን ሆኖ መገኘት ስለሆነ የራስን ሕሊናና ሕልውና መካድ ትልቅ ክህደት ነው:: እኛ ምን አገባን የሚሉ እውነትም ውሸትም አናውቅም ብለው፥ በእንስሳ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው:: ሰው የተፈጠረው ክፉውን ክፉ፥ ጥሩውን ጥሩ ማለት ከሚችል አዕምሮ ጋር ነው:: በዚህ ተፈጥሮ ግንዛቤያችን ይህ ንጽጽር ስንመለከተው የቱ ይከፋል? በፓስተር ዳዊት በኩል ከውጭ የተሰነዘረውን ፕሮቴስታንታዊ ፈተና ጂሀድ ካልነው፥ ከውስጥ የተሰነዘረውን የደፍተራ ገለፈትን ፈተናስ ምን እንበለው?

**ይቆየን**

**ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::**

http://www.medhanialemeotcks.org/